# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነት አጠባበቅን በተመለከተ

## የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2008
አዲስ አበባ

ማውጫ

1. መግቢያ ----------------------------------------------------------------------------------------------1
2. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ራዕይ እና ተልዕኮ -------------------------------3
3. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የፋይናንስ ምንጭ--------------------------------4
4. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር---------------------------------5
5. የአሰራር ስርዓት መግለጫ (የህፃናት መብትና ደህንነት ማስጠበቅ ዳይሬክቶሬት የሥራ ሂደት) (System description---------------------------------------------------------------------6
6. _የኦዲቱ ጭብጦች (Audit Issue) -------------------------------------------------8
7. የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/-----------------------------------------9
8. የህፃናት መብትና ደህንነትን የሚያስጠብቅ ፖሊሲን በተመለከተ-------------------------------11
9. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ መመሪያዎች አተገባበርን በተመለከተ---------------------------12
10. ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናት ወደ ህፃናት ማሳደጊያ አገባብ ሁኔታን በተመለከተ---------------------------------------------------------------------------14
11. ለህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እና ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ግብረ-መልስ የሚደርሳቸው መሆኑን በተመለከተ---------------------------------------------------------------17
12. የህፃናት ማሳደጊያና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ግንኙነት መመሪያን በተመለከተ---20
13. የጉዲፈቻ ህፃናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ የግንዛቤ ሥራ መሰራቱን በተመለከተ--21
14. ወደ ውጭ በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናት የጉብኝት ክትትልን በተመለከተ---------------------------23
15. በጉዲፈቻ ህፃናት ዙሪያ የሚሰሩ ሥራዎች ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ------------------24
16. የጉዲፈቻ ህፃናትን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ--------------25
17. በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ህፃናት ድህረ ጉዲፈቻ ክትትል /Post Placement / ሪፖርትን በተመለከተ-------------------------------------------------------------------------27
18. በውጭ የሚገኙ ኢምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ----------29
19. የሴክተር መ/ቤቶች የህፃናት ጉዳይን በዕቅድና ፕሮግራሞቻቸው አካተው መንቀሳቀሳቸውን በተመለከተ---------------------------------------------------------------------31
20. ከሀገር ውጭ ጉዲፈቻ የተደረጉ ህፃናት መረጃ በተሟላ ሁኔታ ስለመያዙ ክትትል መደረጉን በተመለከተ-------------------------------------------------------------------------32
21. ለውጭ ጉዲፈቻ ብቁ የተባሉ በሀገር ውስጥ አመራጭ ያላገኙ ህፃናትን በተመለከተ--------33
22. በኦዲቱ ወቅት በመልካም ተሞክሮ የታዩ ተቋማትን በተመለከተ--------------------------------34
23. የመደምደሚያ ሀሳቦች-----------------------------------------------------------------------------37
24. የማሻሻያ ሀሳቦች--------------------------------------------------------------------------------40

## መግቢያ

1. የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የኢፌዴሪ መንግሥት የመስሪያ ቤቶችንና አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 471/98 የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ ራሱን ችሎ ተቋቁሞ ኃላፊነቱን ሲወጣ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ተቋሙ ከሴቶች ባሻገርም የሕፃናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ሥራዎችንም እስከ ጥቅምት 2003 ዓ.ም በተጓዳኝ ሲያከናውን ከቆየ በኂላ በፌዴራል ደረጃ የአደረጃጀት ለውጥ መደረጉን ተከትሎ በሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እና በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር በተናጠል የነበረው አደረጃጀት ወደ አንድ እንዲመጣ በመወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 መሠረት የኢፌዴሪ ሴቶች ፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በሚል መጠሪያ በአዲስ መልክ ተቋቁሞ በመንግሥትና በሕዝብ የተጣለበትን አደራ በአግባቡ እየተወጣ ይገኛል፡፡
2. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 36 ለሕፃናት መብቶች ልዩ ትኩረት መሰጠት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ የሕፃናት መብቶች ኮንቬሽን አንቀጽ 3 መሠረት ሕፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ መንግሥታዊም ሆኑ የግል ማህበራዊ ደህንነት ተቋማት፣ ፍ/ቤቶች፣ የአስተዳደር ወይም የሕግ አውጪው አካላት እርምጃ ሲወስዱ የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ማስቀደምና የሚያስፈልገውን ጥበቃና እንክብካቤ ሁሉ የሕፃናትን ጉዳይ በኃላፊነታቸው ታሳቢ እንዲያደርጉ አስቀምጧል፡፡
3. በሀገራችን ወላጅ ያጡና ለችግር ተጋላጭ የሆኑትን ሕፃናት የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅሞ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ መመሪያው በሚፈቅደው መስፈርት መሠረት ሕፃናትን ተቀብሎ ወደ ማሳደጊያ በማስገባት እንዲሁም ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ በአገሮች መካከል እና በአገር ውስጥ የሚደረግ ጉዲፈቻ ወላጅ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
4. ጉዲፈቻ ማለት ከሌላ አብራክ የተገኘን ልጅ ከሌላ ሰው የተወሰደ መሆኑን አምኖና ተቀብሎ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መብቱን ጠብቆ እንደ ገዛ ልጅ አድርጎ ማሳደግ ነው፡፡
5. ጉዲፈቻ ለሚለው ቃል የእንግሊዝኛ አቻው ''adoption'' ሲሆን አመጣጡም 'ad-optare' ከሚል የላቲን ቃል የመጣ ነው፡፡ ትርጉሙም ''መምረጥ'' የሚል ነው፡፡ ይህም ጉዲፈቻ በጉዲፈቻ አድራጊው ምርጫ ብቻ የሚከናወን መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ጉዲፈቻ አድራጊው በነፃ ፈቃዱ ከሌላ አብራክ የተገኘ ልጅ ለማሳደግና ለመጠበቅ እንዲሁም ለእድገቱ አስፈላጊ የሆኑትን ማናቸውንም እንክብካቤ በማድረግ ወስኖ የሚወስደው እርምጃ ሲሆን ይኸም ልጁ የጉዲፈቻ አድራጊውን ቤተሰብ ስም ንብረትና ሕይወት እንዲካፈል የሚያደርግ መብት ያጎናጽፈዋል፡፡ ይህም ማለት ከአብራክ ክፋይ የተገኘ ልጅ ያለውን ማንኛውንም መብት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

6. በሀገራችን ሁለት ዓይነት የጉዲፈቻ አሰጣጥ ሥርዓት ያሉ ሲሆን እነሱም፣ በሀገሮች መካከል እና በአገር ውስጥ የሚደረግ ጉዲፈቻ ሥርዓት ናቸው፡፡ በመሆኑም በሀገሮች መካከል የሚደረግ ጉዲፈቻ ዝምድና በሌላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ የጉዲፈቻ ዓይነት በሚለው ዘርፍ የሚመደብ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ጉዲፈቻ ልጁ የተፈጥሮ ልጅ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን በጉዲፈቻ ተደራጊ መካከል የድንበር፣ የቀለም፣ የባሕል፣ የዘር፣ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነትም ጎልቶ የሚስተዋልበት መሆኑ ነው፡፡
7. በሀገሮች መካከል የሚደረግ ጉዲፈቻ መንግሥት ወላጅ ለሌላቸው ሕፃናት ከሚያቀርበው አማራጭ የእንክብካቤ መንገደች አንዱ ሲሆን ጉዲፈቻው ፐብሊክ (public adoption) በሚለው ዘርፍ ይመደባል፡፡ ይህም ለጉዲፈቻ የሚቀርቡት ልጆች ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው በሚመለከተው የመንግሥት አካል መሆኑን ያመለክታል፡፡
8. ጦርነት፣ በሽታ፣ ድህነት፣ የመሳሰሉት ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ክስተቶች …. በሀገሮች መካከል ለሚደረግ ጉዲፈቻ መስፋፋት አስተዋጽአ አበርክተዋል፡፡ “ በሀገሮች መካከል ለሚደረግ ጉዲፈቻ ” የሚለውን አጠራር በተባበሩት መንግሥታት የዓለም አቀፍ የሕፃናት ፈንድ /ዩኒሴፍ/፣ ልጆች ከትውልድ አገራቸው ድንበር ተሻግረው ወደ ሌላ አገር በመግባት በጉዲፈቻ የሌላ ቤተሰብ አባል የሚሆኑበት ሁኔታ ነው ሲል ይተረጉመዋል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በተለያዩ አገራት ዜጎች መካከል የሚፈጸም ጉዲፈቻ እየጨመረ የመጣው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ በኂላ ነው፡፡ በዚህ ጦርነት የተነሳ አያሌ ሕፃናት ወላጆቻቸውን በማጣታቸው በማሳደጊያዎች ውስጥ በአሰቃቂ ሁኔታ ተይዘው ለማደግ ይገደዱ ነበር፡፡ በሀገሮች መካከል የሚደረግ ጉዲፈቻ የተጀመረው የተለያዩ አገራት ወታደሮች የጦርነት ቀጠና በሆኑ የዓለም አገራት መስፈራቸውን ተከትሎ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡
9. ከጦርነት ግጭት በተጨማሪም ድርቅ፣ በሽታና ድህነትም በሀገሮች መካከል ለሚደረግ ጉዲፈቻ መስፋፋት እንደምክንያት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ለዚህም ሩሲያ፣ ጉዋቲማላ፣ ቻይናና የአፍሪካ አገራት በዚህ ረገድ ስማቸው ከሚነሱት መካከል ይገኙበታል፡፡ በተለይ ከደቡብ ኮሪያ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት በጉዲፈቻ የተወሰዱ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ በሰሜኑና ደቡብ ኮሪያ መካከል በተደረገው በርካታ አገሮች በተስፋፉበት ጦርነት ሳቢያ ልጆች ቤተሰባቸውን በማጣታቸው የተነሳ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በወቅቱ በደቡብ ኮሪያ ሰፍረው ከነበሩ የአሜሪካ ወታደሮች የተወለዱ ሕፃናት በመልክ ከአካባቢው ማህበረሰብ የተለዩ ስለነበሩ ለማህበራዊና ስነልቦናዊ ችግሮች ሲጋለጡ እናቶቻቸውም በሕብረተሰቡ ዘንድ መገለል ይፈጸምባቸው ነበር፡፡ እናም በጦርነት ሰበብ የተወለዱ ሕፃናት እጣፋንነታ በአብዛኛው በጉዲፈቻ ወደ አባቶቻቸው አገር መውሰድ ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በአባታቸው ዜግነት የማግኘት መብት ያላቸው በመሆኑ

የተነሳ ነው፡፡ ይህም በአገሮች መካከል ለሚደረግ ጉዲፈቻ መጨመር የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

10. ከዚህም ባሻገር በጦርነት ምክንያት የተወለዱ ልጆች በመሆናቸው ልንታደጋቸው ይገባል፡፡ የሚለው አሰተሳሰብ በሀገሮች መካከል የሚደረግ ጉዲፈቻን ያስፋፋ ሲሆን፤ በሀገሮች መካከል መልካም ግንኙነት ለመፍጠርም ይረዳል፣ የሚለው አመለካከት ስር መስደዱ ሌላው ምክንያት ነው ሊባል ይችላል፡፡
11. ጉዲፈቻ በኢትዮጵያ በትክክል መቼ እንደተጀመረ የሚጠቁም መረጃ ባይገኝም ከ1800 ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በባሕላዊ መንገድ ይካሄድ እንደነበር ይገመታል፡፡
12. የጉዲፈቻ ዓላማ ከውርስ ሥርዓት ጋር በተያያዘ የዘር ሀረግን ለመቀጠል፣ የዝምድና ትስስርን ለማጠናከር ፖለቲካዊ ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ለማግኘት፣ የሚሉት ከብዙዎቹ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

<u>የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ራዕይ እና ተልዕኮ</u>

***ራዕይ***

13. "የሴቶችና ወጣቶች በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና በባሕላዊ መስኮች እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተረጋገጠባት የሕፃናት መብትና ደህንነት የተከበረባት እና የፆታ እኩልነትን የሰፈነባት ኢትዮጵያን ማየት"

**ተልዕኮ**

14. "የሴቶችና የወጣቶችን እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚኑት በልማት፣ መልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማረጋገጥ፣ የጾታ እኩልነትን ማስፈንና የሕፃናትን መብትና ደህንነት ማስጠበቅ"

**የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የፋይናንስ ምንጭ**


15. የሴቶችና የህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር  የፋይናንስ ምንጭ  ከመንግስት የሚመደብ በጀትና  ከልዩ ልዩ ተራድኦ ሲሆን በጀቱና ሥራ ላይ የዋለው እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡


| ዓ.ም | የበጀት ዓመት | የጸደቀና የተስተካከለ በጀት (ብር) | ሥራ ላይ የዋለ (ብር) | % |
|---|---|---|---|---|
| 2004 | መደበኛ | 18,105,200 | 15,731,921.05 | (86.9%) |
| | ካፒታል | - | - | - |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | 49,980,367 | 35,206,627.40 | (70.44%) |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **68,085,567** | **50,938,548.45** | **74.81%** |
| 2005 | መደበኛ | 21,623,129.23 | 20,457,295.11 | (94.6%) |
| | ካፒታል | - | - | - |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | 41,534,985.66 | 36,849,507 | (86.7%) |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **63,158,114.89** | **57,306,802** | **90.73%** |
| 2006 | መደበኛ | 34,817,704.60 | 31,870,230.97 | (91.53%) |
| | ካፒታል | - | - | - |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | 40,511,633 | 32,520,534 | (80%) |
| | **ጠቅላላ ድምር** | **75,329,338** | **64,390,765** | **85.48%** |
| 2007 (8 months performance) | መደበኛ | 35,418,154.10 | 23,486,178.16 | (66.31) |
| | ካፒታል | - | - | - |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | | | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | 35,418,154.10 | 23,486,178.16 | 66.31 |

## 16. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ሥልጣንና ተግባር

1. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች መብትና ጥቅሞችን በማስተባበር ዙሪያ የግንዛቤ ንቅናቄ እንዲፈጠር ማድረግ፣
2. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ማሳባሰብ፣ ማደራጀት፣ በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ማድረግ፣
3. ሴቶችና ወጣቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤
4. ሴቶች ወጣቶች እንደፍላጎታቸውና እንደችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ማበራታት እና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
5. በፌዴራል መንግሥት አካላት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች የልማት ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት መንደፍ፣ መገምገምና፣ ተገቢውን ክትትል ማድረግ፤
6. በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸት፣ አፈጻጸሙን መከታተል፤
7. በሀገር አቀፍ ደረጃ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት መቀየስና አፈጻጸሙንም መከታተል፤
8. ሴቶች በተለያዩ የመንግሥት አካላት በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤
9. የሕፃናት መብትና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የሚመለከታቸው አካላትን ማስተባበር፤
10. ሴቶችንና ሕጻናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን አፈጻጸም መከታተል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ማቅረብ፤

## 17. የአሰራር ስርዓት መግለጫ (የህፃናት መብትና ደህንነት ማስጠበቅ ዳይሬክቶሬት  የሥራ ሂደት)


የጥናት ውጤቶች
የህፃናት ጥያቄዎች
የባለድርሻ አካላት
ጥናት ማካሄድ
የማስፈፀሚያ ማፅቀፎች/ሰነድ ማዘጋጀትና ማሠራጨት
የትብብርና አጋርነት የመፍጠር ስራዎች
ተቋማት ለህፃናት ሁለንተናዊ እድገት አስፈላጊ አገልግሎቶችን ተደራሽ እንዲያደርጉ የመደገፍ ሥራ
የህፃናት መብቶችን የማስረጽና የህብረተሰብን ተሳትፎ የማሳደግ ስራዎች
የጥበቃ፣የድጋፍና እንክብካቤ ስራዎችን መደገፍ
- የተዘረጋ የህፃናት ጥበቃ ስርዓት
- መሰረታዊ ፍላጎታቸው የተሟላላቸው ህፃናት
- ግንዛቤያቸው ያደገ የህብረተሰብ ክፍሎች
- የህፃናትን ጉዳይ ሜይንስትሪም ያደረጉ ተቋማት
- የተፈጠረ ትብብርና ቅንጅት
ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ
-ለህጻናት መብትና ደህንነት የቆሙ የህብረተሰብ ክፍሎች
-መብትና ደህንነታቸው የተጠበቀላቸው ህፃናት


ወደ ተግባር የተሸጋገሩ የማስፈፀሚያ መሳሪያዎች፤ ጋይድላይኖች፤ ኮንቬንሽኖችና ስምምነቶች እና የተቀመጡ ግቦችና ዕቅዶች፤ የተሰጡ ስልጠናዎች የተደረጉ የድጋፍ ስራዎች
ክትትልና ግምገማው የሚካሄድበትን አካልና ጉዳይ መለየት
ውሳኔ
ግምገማ የሚረዱ ቢጋር፣ ቼክሊስትና ፎርማት ማዘጋጀት
ቢጋር ማዘጋጀትና ውል
የመስክ ግምገማ ማካሄድ
በአማካሪ የሚዘጋጁ ቼክሊስቶችና ፎርማቶች በአስተያት
በመስክ የተገኙ መረጃዎችንና ከፈጻሚ አካላት የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን ማጠናቀር
ክትትልና ድጋፍ
የተገኙ ውጤቶችን የጋራ መድረክ በማዘጋጀት መገምገም
በቢጋሩ መሰረት መስራቱን በቡድን አስተያየት መስጠትና እንዲስተካከል ማድረግ
የተዘጋጀውን/የተጠናቀረውን የክትትልና ግምገማ ሪፖርት ለሚመለከተው አካላት ማሰራጨት እንዲሁም ለቀጣይ ስራ ግብዓት
ሪፖርቱን ማሰራጨት/ግብረ መልስ በማዘጋጀት ለቀጣይ ስራ ግብዓት እንዲሆን

**የኦዲቱ አላማ ፡-**

18. የኦዲቱ ዋና ዓላማ  የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የጉድፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነት አጠባበቅ ስርዓት፤ ክትትልና አፈጻጸም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው መመሪያዎች መሰረት  ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ በብቃት እና በቁጠባ የሚከናወን ፣ አላማውንም ማሳካቱን እና  ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን፤ በክዋኔ ኦዲቱ የተለዩ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮችን  ለማሻሻል የሚረዱ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

**የኦዲ አካባቢ**

19. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ /Potential Audit Area/ የጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነት አጠባበቅ ስርዓት፣ ክትትል እና አፈፃፀም  በሴቶቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በሚገባ መተግበሩን መገምገምን የሚመለከት ነው፡፡

**የኦዲቱ ጭብጦች (Audit Issue)**

20. በተመረጡ የኦዲት አከባቢ (Potential Audit Area) ሥር 3 (ሶስት) የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) እና አንድ ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ /sub Audit Issues / ተለይተዋል፡፡ እነሱም ፡-

    1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሮች መካከልና በሀገር ውስጥ የሚደረግ ጉዲፈቻ አሰጣጥ የህፃናት መብትና ደህንነትን ለማስጠበቅ  እና ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን ሊፈታ የሚችል ፖሊሲ፣ አዋጁን መሰረት ያደረገ መመሪያ አውጥቶ አፈፃፀማቸውን የሚክታተል፣ የሚገመግምና የግብረ መልስ አሰራር ሥርዓት (system) ዘርግቶ በኢኮኖሚ ፣ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተገበረ መሆኑን ማጣራት፤
    2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነትን ለማስጠበቅ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ጠቀሜታን ባገናዘበ መልኩ ከጉዲፈቻ አስፈጻሚ ኤጀንሲዎችና

ከባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋ እና ውጤታማ ቅንጅታዊ አሠራር የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማጣራት፤

2.1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየደረጃው ላሉ ባለድርሻ አካለት የስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ አሰጣጥ ስርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ በማድረግ ያመጣውን ውጤት የሚገመግም መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

3. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነት አጠበበቅን በተመለከተ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፡፡

## <u>የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች /Evaluative Criteria/</u>

21. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሶስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫና አንድ ንዑስ የትኩረትአቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 33 (ሰላሳ ሶስት) የመመዘኛ መስፈርቶች / Evaluative Criteria/ የተዘጋጁ ሲሆን፤የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የሚኒስቴር መ/ቤቱ መቋቋሚያ አዋጅ፣ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸው መመሪያዎች ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መስጫ መመሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/፣ለድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መምረጫ መሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/ ፣ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ለሚሰጧቸው የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች/Standards Sene 2004/ ፣ አማራጭ የህፃናት ክብካቤ መመሪያዎች በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ የህፃናት ክብካቤ መልሶ የማቀላቀልና ዳግም የማዋሃድ ፕሮግራም የፎስተር ክብካቤ የጉዲፈቻ እና የህፃናት ማሳደጊያ አገልግሎት/ ሰኔ 2001 ዓ.ም ፣ የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር፣ በአገሮች መካከል የሚደረግ የጉዲፈቻ አገልግሎት አገልግሎት አሰጣጥ የውስጥ አሰራር መመሪያ/ግንቦት 2000 ዓ.ም/፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ደብዳቤዎች ፣ከ 2004- 2007 ዓ.ም የተዘጋጁ የእቅድ አፈፃፀሞች፣ የቢፒ አር ጥናት እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ በተዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸዋል፡፡ መመዘኛ መስፈረቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

**<u>የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ</u>**

22. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በሴቶች፣ ወጣቶችና ሕፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር ሲሆን፤ እንዲሁም ለኦዲቱ በናሙና በተመረጡ  አራት በአዲስ አበባ መስተዳድር በሚገኙ የህፃናት ማሳደጊያዎች፡-

- ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን፤ ትኩል ኤስ ኦ ኤስ ፣ ኪዳነ ምህረት/በካቶሊክ ቤተክርስቲያን/ እና አድገት የህፃናት ማሳደጊያ ማህበር በተጨማሪም አራት የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች አሜሪካን ወርልድ ፣ ኩዊን ኦፍ ሜርሲ ፣ መንዲ አሶሴሽን አዶፕታ እና ቢታኒ
- በኦሮሚያ ክልል ፡- በሰበታ ብርሃን ፋሚሊ ዌልፈር ፋውንዴሽን ፣ በገላን ኤስ ኦ ኤስ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም  እና በሞጆ ራፊኪ ፋውንዴሽን ህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት፣
- በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፡- አጁጃ ህፃናት ማሳደጊያ ፣ ሀዋሳ ህፃናት ማሳደጊያ፣ ሀዋሳ አቤነዘር ስፖርቲንግ ዴቨሎፕመንት ህፃናት ማሳደጊያ ፣
- በሀረሪ ክልል፡- እንግዳ ህፃናት ማሳደጊያ
- በድሬዳዋ መስተዳድር፡- አቤነዘር የህፃናት ማሳደጊያ ተቋም፣ ብርሃን ፋሚሊ ዌልፈር ፋውንዴሽን ሲሆኑ፣

የክልል/ከተማ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች

- የኦሮሚያ ክልል የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ፣ በኦሮሚያ የሰበታ፣ ገላን እና ሞጆ ከተማ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች፣
- በደቡብ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የክልሉ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ እና የሀዋሳ ከተማ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ
- በሀረሪ ክልል፡- የክልሉ ሴቶችና ህፃናት ጉዳ ቢሮ
- በድሬዳዋ መስተዳድር የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ እና
- በአዲስ አበባ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ  ከ 2004 እስከ 2007 ዓ.ም ባለት አራት የበጀት ዓመታት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸው የህፃናት መብትና ደህንነት አጠባበቅ ስርዓት፣ ክትትልና አፈፃፀም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ኖሮት ተፈፃሚ መሆኑ ላይ በማተኮር ነው፡፡ ኦዲቱም የተከናወነው የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት፣ የክልል/ ከተማ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ፣ የህፃናት ማሳደጊያ እና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና በችግሮቹ ዙሪያ በመወያየት፤ በጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነት አጠባበቅ ስርዓት፣ ክትትልና

አፈፃፀም ጋር ተያያዥ የሆኑ እና አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመከለስና አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በማየት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲቱ ግኝቶች

<u>የህፃናት መብትና ደህንነትን የሚያስጠብቅ ፖሊሲን በተመለከተ</u>

23. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት መብትና ደህንነትን የሚያስጠብቅ ፖሊሲ አውጥቶ በሚመለከተው አካል ሊያፀድቅ ይገባል፡፡

24. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት መብትና ደህንነት የሚያስጠብቅ በ ሚያዚያ 2003 ዓ.ም የመጨረሻ ብሔራዊ ረቂቅ የህፃናት ፓሊሲን አዘጋጅቶ ያቀረበ መሆኑ ቢታወቅም፤እንዲፀድቅ ለማድረግ ያደረጋቸው ጥረቶች ባለመኖራቸው ይህ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት እስከ 2008 ጊዜ ድረስ ያልፀደቀ ሲሆን በተጨማሪም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት መብትና ደህንነት ማስጠበቅ ዳይሬክቶሬት በ 2004 ዓ.ም ባወጣው የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በብሄራዊ የህፃናት ፖሊሲው አለመፅደቅ ምክንያት ለ 1.5 ሚሊዮን ህዝብ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ለመስጠት ታቅዶ ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

25. ስለ ሁኔታው የህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ፖሊሲ የማፀደቅ ሂደት የብዙ ባለድርሻ አካላትን ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ በተፈጥሮው በአጭር ግዜ መጠናቀቅ የማይችል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

26. ኃላፊው በሰጡት መልስ ፖሊሲ ማፀደቅ እረጅም ግዜ የሚፈጅ ነው ቢሉም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፖሊሲውን ከማፀደቅ አንፃር ያደረጋቸውን ሙከራዎች እና ለምን አምስት ዓመት እንደ ወሰደበት የሚያሳዩ መረጃዎች ባለ ማቅረቡ ተአማኒነት አላገኘም፡፡

27. በኦዲቱ ወቅት መገንዘብ የተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ 2003 ዓ.ም ያዘጋጀውን የመጨረሻ ረቂቅ የህፃናት ፖሊሲ ለማፀደቅ ከፍተኛ ጥረት ባለማድረጉ አምስት ዓመታት በማስቆጠሩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዘጋጀው ፖሊሲ አለመፅደቅ ምክንያት ከፖሊሲው የሚገኙ ጥቅሞችን የሀገሪቱ ህፃናት እንዳያገኙ አድርጓል፡፡

<u>በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ መመሪያዎች አተገባበርን በተመለከተ</u>

28. ሁሉም የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ መመሪያዎችን ከመተግበር አንፃር ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

29. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ መመሪያዎች፡- በናሙና ተመርጠው በታዩ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እንዲተገበሩ በተሟላ ሁኔታ የተሰራጩ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፤

***መመሪያዎች***

ሀ. ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መስጫ መመሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/

ለ. ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡ ና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መምረጫ መመሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/

ሐ. የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ለሚሰጧቸው የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች/Standards Sene 2004/

መ. አማራጭ የህፃናት ክብካቤ መመሪያዎች በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ የህፃናት ክብካቤ መልሶ የማቀላቀልና ዳግም የማዋሃድ ፕሮግራም የፎስተር ክብካቤ የጉዲፈቻ እና የህፃናት ማሳደጊያ አገልግሎት/ ሰኔ 2001 ዓ.ም/ እና

ሠ. የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር

**ቀጥሎ ለተመለከቱት የህፃናት ማሳደጊያዎች በተሟላ ሁኔታ ያልተሰራጩ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት መረዳት ተችሏል፡፡**

- ሞጆ ራፊኪ ፋውንዴሽን ህፃናት ማሳደጊያ ፡- ከላይ የተገለፁት አንዳቸውም የሌለው መሆኑ፣
- ገላን ኤስ ኦ ኤስ የህፃናት ማሳደጊያ አንዳቸውም የሌሉት መሆኑ፣
- ሀዋሳ አጁጃ ህፃናት ማሳደጊያ፡- ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መምረጫ መመሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/ እና የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር  የሌለው መሆኑ፣
- ሀዋሳ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም፡- ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መምረጫ መመሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/ እና የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር  የሌለው መሆኑ፣
- ሀዋሳ አቤነዘር ስፖርቲንግ ዴቨሎፕመንት፡-ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ወላጅ ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መምረጫ
- መመሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/ እና የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር  የሌለው መሆኑ፣
- ድሬዳዋ ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን ፡- ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መስጫ መመሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/ በስተቀር ሌሎቹ የሌሉት መሆኑ፣

- ሀረሪ ክልል እንግዳ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋም፡- የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ለሚሰጧቸው የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች/Standards Sene 2004 በስተቀር ሌሎቹ የሌሉት መሆኑ፣
- ድሬዳዋ አቤነዘር ህፃናት ማሳደጊያ፡- ከ ወላጆቻቸውን ላጡና ተጋላጭ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መስጫ መመሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/በስተቀር ሌሎቹ የሌሉት መሆኑ፣
- አዲስ አበባ ኤስ ኦ ኤስ ትኩል ህፃናት ማሳደጊያ፡- ከአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር በስተቀር ሌሎቹ የሌሉት መሆኑ፣
- አዲስ አበባ ብርሃን ፋሚሊ ዌልፈር ፋውንዴሽን ፡- ከህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ለሚሰጧቸው የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች /Standards Sene 2004/ በስተቀር ሌሎቹ የሌሉት መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ኪዳነ ምህረት ህፃናት ማሳደጊያ፡- ከድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መምረጫ መመሪያ /የካቲት 2002 ዓ.ም/ በስተቀር ሌሎቹ የሌሉት መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ እድገት የህፃናት ማሳደጊያ ማህበር፡- ከላይ ከተገለፁት አንዳቸውም የሌሉት መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ለህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እና ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች በአቀረበው ቃለ-መጠይቅ ከተሰጠ መልስ እና በመስክ በተደረገ ምልከታ ማወቅ ተችሏል፡፡

30. እንዲሁም ለማሳያ ከመመሪያዎቹ አንዱ የሆነው የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ለሚሰጧቸው የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች /Standards Sene 2004/ በገላን ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም የሌለ በመሆኑ በህፃናት ማሳደጊያው የሚሰጠው የምግብ አገልግሎት የስጋና የአትክልት አቅርቦት የሌለው መሆኑ እና የንፅህና መጠበቂያ ሳሙና በቁጥር አንድ የሆነን ለስድስት የመጠቀም ሁኔታ ያለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት እድሜያቸው ከ 14 ዓመት በላይ ለሆኑ ህፃናት የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ማወቅ ተችሏል፡፡
31. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸው መመሪያዎች ለህፃናት ማሳደጊያ ተቋማቱ በሚገባ ስለ አለልደረሱበተ ሁኔታ በናሙና ተመርጠው የታዩ የህፃናት ማሳደጊያ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከላይ በቅደም ተከተል በተቀመጠው መሰረት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በተሟላ ሁኔታ እንዲደርሳቸው ባለ መደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡
32. በማጠናከሪያ መልኩም በሚኒስቴሩ መ/ቤት የህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለ ጉዳዩ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ መመሪያዎች ተዘጋጅተው

ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ በመስጠቱ ከዚህ በፊት ወጥነት የሌላቸው አሰራሮች ስርዓት እንዲይዙ የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

33. ሆኖም ኃላፊው ይህን ቢሉም በኦዲቱ ወቅት መገንዘብ የተቻለው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ከተሰጡት ተግባራት የሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶች መብትና ጥቅሞችን በማስተባበር ዙሪያ የግንዛቤ ንቅናቄ እንዲፈጠር ማድረግ፣ የህፃናት መብትና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የሚመለከታቸው አካላትን ማስተባበር፣ የሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች መሰብሰብ፣ማደራጀትና በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ማድረግ እና ሴቶችንና ህፃናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን አፈፃፀም መከታተል እና ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ማድረግ፤ ከሚለው ኃላፊነትን መወጣት አንፃር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸው ከላይ የተገለፁት የተለያዩ መመሪያዎች በህፃናት ማሳደጊያ ተቋማቱ በተሟላ ሁኔታ ባለመገኘታቸው ለወጥነት አሰራር አስተዋፆ አለማድረጋቸውን በኦዲቱ ወቅት መረዳት ተችሏል፡፡

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸው መመሪያዎች በተሟላ ሁኔታ ለህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ተሰራጭተው አለመገኘታቸው በተቋማቱ ውስጥ ወጥ አሰራር እንዳይኖር አስተዋፆ ያደርጋል፡፡

<u>ወላጆቻቸውን ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናት ወደ ህፃናት ማሳደጊያ አገባብ ሁኔታን በተመለከተ</u>

35. ሁሉም የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የህፃናት አቀባበልና ምደባን በተመለከተ ወጥ የሆነ መመሪያ እና አሰራር ስርዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

36. ሆኖም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በሰበታ ብርሃን ፋሚሊ ዌልፈር ፋውንዴሽን፤ በገላን ኤስ ኦ ኤስ፣በሞጆ ራፊኪ ፋውንዴሽን፣ በደቡብ አጃጃ ህፃናት ማሳደጊያ፣ ሀዋሳ ህፃናት ማሳደጊያ፣ ሀዋሳ አቤነዘር ስፖርቲንግ ደቨሎፐመንት፣ሀረሪ እንግዳ ህፃናት ማሳደጊያ፣ ድሬዳዋ አቤነዘር ፣ ድሬዳዋ ብርሃን ፋሚሊ ዌልፈር፣ አዲስ አበባ ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን፣ አዲስ አበባ ትኩል ኤስ ኦ ኤስ፣ኪዳነ ምህረት እና አዲስ አበባ እድገት የህፃናት ማሳደጊያ ማህበር ሁሉም በሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የተዘጋጀውን ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መምረጫ መመሪያ /የካቲት 2002 ዓ.ም/ ህፃናትን በመምረጥ ሂደት ላይ መሳተፍ የሚኖርባቸው አካላት፡-

1. የቀበሌ / ወረዳ መስተዳድር ተወካይ -------------------------- ሰብሳቢ
2. የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ተወካይ------------- ም/ሰብሳቢ
3. የቀበሌው /ወረዳው የጤና ኤክስቴንሽን ተወካይ------------------- ፀሐፊ
4. በቀበሌው /ወረዳው ውስጥ ድጋፍ የሚሹ ህፃናት ተወካይ--------- አባል

5. በቀበሌው /ወረዳው ውስጥ ያለ ት/ቤት ተወካይ------------------- አባል
6. ድጋፉን የሚሰጥ የበጎ አድራጎት ድርጅት------------------------- አባል
7. የቀበሌው /ወረዳው ሴቶች ማህበር ተወካይ ----------------------- አባል
8. በቀበሌው/ወረዳው ውስጥ የሚንቀሳቀስ ጠንካራ እድር ተወካይ - አባል
9. በቀበሌው/ወረዳው ውስጥ ከሚገኙ የሃይማኖት ተቋማት ተወካይ-- አባል
10. በቀበሌው/ወረዳው የሚገኙ አረጋውያን ማህበራት ተወካይ ----------- አባል
11. በቀበሌው/ወረዳው የህፃናት ፓርላማ ተወካይ ------------------------- አባል
12. በቀበሌው የህፃናት መብት ኮሚሽን /ሲ አር ሲ/ አባል ተወካይ ---------አባል
13. ኤች አይ ቪ በደማቸው የሚገኙባቸው ማህበራት ተወካይ-------------- አባል
14. የወላጆቻቸውን ያጡና ተጋላጭ የሆኑ ህፃናት ተወካይ ---------------- አባል

መሳተፍ የሚገባቸውን 14 አካላትን ድጋፉን የሚሰጠውን የበጎ አድራጎት ድርጅቱን ጨምሮ በዝርዝር ያስቀመጠ ቢሆንም የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች በዝርዝሩ ውስጥ እንደ አንድ አካል የተካተቱ ሆነው መመሪያው በእጃቸው ሳይኖር እና መሳተፍ የሚገባቸውን አካላት ሳያሳትፉ ህፃናትን ወደ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም በሸኚ ደብዳቤ የሚመድቡ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል ።ለማሳያ የድሬዳዋ፣የሀረሪ እና የአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃት ቢሮዎች እንዲሁም በከተማ ደረጃ የሰበታ፤ የገላን እና የሞጆ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች፤ህፃናትን ወደ ማሳደጊያ ተቋማት በደብዳቤ ሸኚነት ማስገባታቸው በኦዲቱ በናሙና ከታዩ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች ካቀረቡአቸው ማስረጃዎች መረዳት ተችሏል።

37. በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መምረጫ መመሪያ መሰረት በትክክል ህፃናት ወደ ማሳዳጊያ ተቋማት መግባታቸውን በመስክ በመገኘት ግምገማ በማድረግ የማይከታተል መሆኑ ታውቋል።

38. ስለ ሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ- መጠይቅ በሰጡት መልስ የድሬዳዋ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ህፃናት ማሳደጊያ እንዲያቀይ የተሰጠውን እና የተለየ አስገዳጅ ሁኔታ የገጠማቸውን ህፃናት ተቀብሎ በህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እንክብካቤ እንዲያገኙ የሚያደርግ መሆኑን፣ የሀረሪ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ወደ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም የሚያስገባቸው መንገድ ላይ የተጣሉ ህፃናትን በፖሊስ ጉዳያቸው የተጣራውን እና ጥቃት የደረሰባቸውን በህፃናት መብት ኮሚሽን (ሲ አር ሲ) እና በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ሸንጎ የተጣራ መረጃ ያላቸውን ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ወደ ተቋማት የሚገቡ ህፃናት ከወረዳ ጀምሮ ማስረጃቸው በተጣራ ሁኔታ የቀረበላቸውን ማስረጃዎችን በማገናዘብ የሚያስገቡ መሆኑን ገልፀዋል።

39. በከተማ ደረጃ በሰበታ የከተማው ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊዎች ህፃናትን በህፃናት መብት ኮሚሽን (ሲ. አር ሲ.) በተፃፈ ደብዳቤ እና ተጥለው የተገኙ ህፃናትን ፖሊስ በሚያቀርበው ማስረጃ መሰረት ህፃናት ማሳደጊያ የሚመድቡ መሆኑን ገልፀው፤በከተማው ውስጥ እነርሱ በማያውቁት ሁኔታ ውል ሳይኖረው ያለምንም እውቅና እየሰራ የሚገኝ የኮሪያ ህፃናት ማሳደጊያ የተባለ አስር ህፃናትን ይዞ የሚገኝ መኖሩን፤ እነዚህን ህፃናት ከየት እንደወሰዳቸው መረጃ የሌላቸው በመሆኑ ስለ ህፃናቱ ሁኔታ መከታተል ያልቻሉ መሆኑን ሲገልፁ የገላንና ሞጆ ከተማ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊዎች ህፃናትን በህፃናት መብት ኮሚሽን (ሲ. አር ሲ.) ማስረጃ የሚመደቡላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

40. እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ህፃናት ወደ ህፃናት ማሳደጊያ በትክክል መግባት አለመግባታቸው የሚረጋገጠው ህፃናት ማሳደጊያው በሚገኝበት ክልል ስልጣን ባለው ዘርፍ ሲሆን፤ ይሁን እንጂ በተጠቀሰው ሁኔታ ህፃናት የሚኒስቴር መ/ቤቱን አገልግሎት ፈልገው በሚመጡበት ጊዜ የሚያቀርቡትን ማስረጃ በማየት በትክክል ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም መመደብ አለመመደባቸውን የሚያረጋግጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊ ይህን ቢሉም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው መመሪያ መሰረት ህፃናት 14 አካላትን ባካተተ ሁኔታ ተመርጠው ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም አለመግባታቸውን እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም በአዋጅ ከተሰጠው ስልጣንና ተግባር አንፃር የህፃናት መብትና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የሚመለከታቸው አካላትን የማስተባበር ተግባር የተጣለበት በመሆኑ ይህን በመስክ ክትትል በማድረግ በራሱም ሆነ በክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች እንዲተገበር አለማድረጉን በሚያሳይ ሁኔታ ህፃናት የመ/ቤቱን አገልግሎት ፈልገው ሲመጡ ከሚያቀርቡት ማስረጃ ብቻ በማየት በትክክል መመደብ አለመመደባቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑን መግለፁ ያወጣውን መመሪያ አተገባበር ቁጥጥርና ክትትል የማያደርግ፤እንዲሁም በአዋጅ የተሰጠውን ተግበር ያልተወጣ መሆኑን የሚያመለክት በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ታምኖበታል፡፡

42. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጀውን የህፃናት ወደ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም መግቢያ መመሪያ እንዲተገበር ክትትል አለማድረጉ እና በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር አለመተግበሩ ወላጆቻቸውን ላጡና ለችግር ተጋላጭ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ለመስጠት በሚደረገው ህፃናቱን የመምረጥ ሂደት ግልፅነት እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ አገልግሎቱ የሚገባቸው ህፃናት አገልግሎቱን እንዳያገኙ የሚያደርግ ሲሆን ማግኘት የማይገባቸው እንዲያገኙ በር ይከፍታል፡፡

**ለህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እና ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ግብረ-መልስ የሚደርሳቸው መሆኑን በተመለከተ**

43. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እና ከጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ለሚቀርብለት የሩብ ዓመት ሪፖርትን መሰረት በማድረግ ለሚያቀርቡት ዓመታዊ ሪፖርት እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው የህፃናት ማሳደጊያ እና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች መገምገሚያ ቼክ ሊስቶች መሰረት ግምገማ ለተደረገላቸው ግብረ-መልስ ሊሰጥ ይገባል፡፡

44. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ

- በሰበታ ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን ከ 2004 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ ላቀረቡት ሪፖርት በሚመለከታቸው ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች በቃል ከማድነቅ ውጭ በፅሁፍ ያልተሰጠ መሆኑን፣
- በገላን ኤስ ኦ ኤስ ህፃናት ማሳደጊያ ከ 2004- 2007 ዓ.ም ድረስ ላቀረቡአቸው ሪፖርቶች በሚመለከታቸው ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች ግብረ-መልስ ያልተሰጠ መሆኑን፣
- በሞጆ ራፊኪ ፋውንዴሽን ለሚያቀርቡአቸው ሪፖርቶች ግብረ-መልስ በሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ አለመሰጠቱን፤
- በደቡብ ሀዋሳ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ፍቃድ ካገኘበት ግዜ ጀምሮ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው መገምገሚያ ቼክ ሊስት ያልተገመገመ መሆኑ፣
- ሀረሪ እንገዳ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባሉት ግዜያት ላቀረቡአቸው ሪፖርቶች፣ እንዲሁም ለተደረገላቸው ግምገማ ግብረ-መልስ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- ድሬዳዋ ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን የድሬዳዋ መስተዳድር ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ሰራተኞች መጥተው ቢገመግሙም የፅሁፍ ግብረ-መልስ የማይሰጡ መሆኑ፣
- በድሬዳዋ መስተዳድር አቤነዘር ህፃናት ማሳደጊያ ከ 2004- 2007 ዓ.ም ላቀረቡአቸው ሪፖርቶች እና ለተደረገው ግምገማ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ግብረ-መልስ ያልሰጠ መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ኤስ ኦ ኤስ ትኩል ህፃናት ማሳደጊያ ከ 2004- 2007 ዓ/ም ድረስ ላቀረቡአቸው ሪፖርቶችና አንድ ግዜ ለተደረገ ግምገማ ግብረ-መልስ ያላገኙ መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ ላቀረቡት ሪፖርቶች ግብረ-መልስ ያገኙ መሆኑን ቢገልፁም ግምገማን በተመለከተ ተገምግመው የማያውቁ መሆኑን፣

- ❖ በአዲስ አበባ ኪዳነ ምህረት/ካቶሊክ/ ህፃናት ማሳደጊያ ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ ከአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮም ሆነ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ መጥተው ግምገማ ከማድረግ በስተቀር ጠንካራና ደካማ ሁኔታዎችን በሚገልፅ መልኩ ግብረ-መልስ ሰጥተው የማያውቁ መሆኑን፣
- ❖ እንዲሁም በአዲስ አበባ እድገት የህፃናት ማሳደጊያ ማህበር ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ ላቀረቡአቸው ሪፖርቶች እና በ 2006 ዓ.ም ለተደረገ ግምገማ ግብረ-መልስ አለማግኘታቸውን ገልፀዋል፡፡

የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎችን በተመለከተ በናሙና በታዩት አራት ኤጀንሲዎች፡-

- በአሜሪካ ወርልድ ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ አንዴ የተገመገሙ ቢሆንም ውጤቱን የሚያሳይ ግብረ-መልስ ያላገኙ መሆኑ፣
- ኩዊን ኦፍ ሜርሲ ከ 2004- 2007 ዓ.ም ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሁለት ግዜ የተገመገመ ቢሆንም ግብረ-መልስ ያልተሰጠው መሆኑን፣
- ቢታኒ ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲ ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ የተገመገመ መሆኑ ቢገለፅም ግብረ-መልስ ያልተሰጠው መሆኑ
- አሶሴሽን ኦፍ መንዲ አዶፕታ ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ ስለ መገምገሙ የሚያመለክት ግብረ-መልስ የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

45. በናሙና ተመርጠው የታዩ ሁሉም የህፃናት ማሰደጊያዎች እና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባሉት ግዜያት ላቀረቡአቸው ሪፖርቶችና በተቋሞቻቸው ለተደረጉ ግምገማዎች ግብረ-መልስ ያገኙ ስለመሆናቸው በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ግብረ-መልስ ያልተሰጣቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡
46. ስለ ጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ መሰረት ቼክ ሊስት እና ገምጋሚ ቡድን በማዘጋጀት በሥራ ላይ የሚገኙ ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቶች እና የህፃናት ማሳደጊያዎችን ግምገማ በማድረግ የተገኘ ውጤት ላይ በሁሉም ገምጋሚ ቡድን መስማማት ላይ ተደርሶ ውጤቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ የሚደረግ መሆኑን፤ እንዲሁም በተገኘው ውጤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የምክክር መድረክ የሚዘጋጅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
47. በተጨማሪም ዳይሬክተሩ በ 17/06/ 2008 ዓ.ም ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ 64 የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቶች ጥር 2005 ዓ.ም የሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ፣ የህዝብ ተወካዮች የሴቶችና ወጣቶች ኮሚቴ

በተገኙበት  የተገመገሙ ስለ መሆናቸው የሚገልፅ 2 ጥራዝ 290 ገፆች የያዘ ረቂቅ ሪፖርት/ ባለፉት ሶስት ዓመታት ያልፀደቀ እና በማህተም ውሳኔው ያልተደገፈ/ ያቀረቡ ሲሆን፤ በተናጠል ለጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች የግምገማ ሪፖርትን ማሳወቅን በተመለከተ በ 15/08/05 ዓ.ም ለአሶሴሽን መንዲ አዶፕታ፣ በ 16/08/05 ለአሜሪካ ወርልድ አዶፕሽን አሶሴሽን፣ በ 16/08/05 ለቢታኒ ክርስቲያን ሰርቪስ፣ በ 16/08/05 ለዳን አዶፕሽን በላኩዋቸው ደብዳቤዎች ያሳወቁ ስለመሆናቸው ገልጸዋል ፡፡

48. እንዲሁም የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማትን በተመለከተ  የመከታተልና እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ያለው የክልል አካል መሆኑን አመላክተው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከህፃናት መብትና ደህንነት አንፃር ስታንዳርድ ማዘጋጀት ፣ በስታንዳርዱ ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግና በጥናት ላይ ተመስርቶ ያገኛቸውን ክፍተቶች ለክልሎች  ማሳወቅና ድጋፍ ማድረግ  ካልሆነ በስተቀር እርምጃ የመውሰድ ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

49. ይሁን እንጂ ኃላፊው ከላይ የተመለከተውን  ሀሳብ ቢገልፁም በኦዲቱ ወቅት መረዳት የተቻለው በናሙና ተመርጠው የታዩት የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ከተሰጠው ተግበር አኳያ፡-

- የህፃናት መብትና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የሚመለከታቸውን ያስተባብራል፣
- እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተቀመጠው የአሰራር ስርዓት መግለጫ ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ የማካሄድ የሥራ ፍሰት፡- ለግምገማ የሚረዱ ቢጋር፣ ቼክ ሊስትና ፎርማት ማዘጋጀት፣ የመስክ ግምገማ ማካሄድ፣ በመስክ የተገኙ መረጃዎችንና ከፈፃሚ አካላት የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ማጠናከር፣ የተገኙ ውጤቶችን የጋራ መድረክ /ክልሎችንም ይጨምራል/ በማዘጋጀት መገምገም፣ የተዘጋጀውን/ የተጠናከረውን የክትትልና ግምገማ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፤ ግብረ መልስ በማዘጋጀት ለቀጣይ ሥራ ግብዓት እንዲሆን ማድረግ

ከሚሉት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአሰራር ስልት ንድፍ አንፃር የህፃናት ማሳደጊያ ተቋሚት የሚኒስቴር መ/ቤቱን ትኩረት የሚሹ በመሆኑ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማትን በተመለከተ ከግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ውጪ ያለው ኃላፊነት የክልሎች ጉዳይ እንጂ እኛን አይመለከተንም መባሉ ተቀባይነት የለውም፡፡

50. የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ግብረ-መልስ ያልደረሳቸው መሆኑን መግለፃቸውን በተመለከተ በድራፍት የቀረበውን ውሳኔ ያለገኘ 2 ጥራዝ ባለ 290 ገፅ ሰነድ ባለመቀበል  በተናጠል

ለጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎቹ የተላኩትን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው የጉዲፈቻ አስፈፃሚዎች መገምገሚያ ቼክ ሊስት መሰረት ያልተገመገመና በመቶኛ ውጤቱ ያልተቀመጠ በመሆኑ እና የመጨረሻውን የውሳኔ ሃሳብ ብቻ በሚያሳይ መልኩ በመገለፁ በከፊል በጥር ወር 2005 ዓ.ም ብቻ የተገመገመ በማስረጃ የተደገፈ በሚል ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ ሆናም ግምገማው በ 2006 ዓ.ም እና በ 2007 ዓ.ም በቀጣይነት ያልተገረገ መሆኑን ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

51. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያዘጋጃቸው የህፃናት ማሳደጊያ እና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች መገምገሚያ ቼክሊስቶችን ተግባራዊ በማድረግ ወይም በማስደረግ፤ እንዲሁም በየደረጃው ለሚገኙ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎችም ሆነ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች የግብረ-መልስ ስርዓት እንዲተገበር ክትትል አለማድረጉ ወይም አለማስደረጉ በአሰራር/አተገባበር ሂደት ውስጥ ተጠያቂነት ለሌለው አሰራር በር ከፋች ይሆናል ፡፡

**<u>የህፃናት ማሳደጊያና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ግንኙነት መመሪያን በተመለከተ</u>**

52. የህፃናት ማሳደጊያና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ስለሚኖራቸው ግንኙነትና እና ትስስር ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

53. መመሪያው ስለ መዘጋጀቱ ኦዲት ሲደረግ፤ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መመሪያው ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

54. በተጨማሪም መመሪያው ባለመዘጋጀቱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በናሙና ተመርጠው በታዩ 13 ህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በሰበታ ብርሃን ፋሚሊ ዌልፌር ፋውንዴሽን፣ በገላን ኤስ ኦ ኤስ፣ በሞጆ ራፊኪ ፋውንዴሽን ፣ በደቡብ አጁጃ ህፃናት ማሳደጊያ፣ ሀዋሳ ህፃናት ማሳደጊያ፣ ሀዋሳ አቤነዘር ስፖርቲንግ ዴቨሎፕምንት፣ ሀረሪ እንግዳ የህፃናት ማሳደጊያ፣ ድሬዳዋ አቤነዘር ህፃናት ማሳደጊያ፣ ድሬዳዋ ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን፣ አዲስ አበባ ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን፣ ትኩል ኤስ ኦ ኤስ ህፃናት ማሳደጊያ፣ ኪዳነ ምህረት ህፃናት ማሳደጊያና እድገት ማህበር ህፃናት ማሳደጊያ እና 4 የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች አሜሪካን ወርልድ፣ ኩዊን ኦፍ ሜርሲ፣ አሶሴሽን ኦፍ መንዲ አዶፕታና ቢታኒ መካከል የሚደረግ የ ሥራግንኙነት ውል የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

55. ሆኖም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ውስጥ ለማሳያ በሀዋሳ አጁጃ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም እና በኢንተርናሽናል ኤት መካከል በተደረገ ውል በዓመት ለውጭ ጉዲፈቻ 130 ህፃናትን ማቅረብ የሚል ስምምነት የተደረሰበት ሰነድ ለመመለከት የተቻለ በመሆኑ ህፃናት በከፍተኛ ደረጃ ለጥቅም ትስስር ሊውሉ እንደሚችሉ ያመላክታል ፡፡

56. በናሙና ተመርጠው የታዩ ሁሉም የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማትና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች በመካከላቸው የሚደረግ የሥራ ግንኙነት ውል በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚታወቅ ስለ መሆኑ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የማይታወቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

57. ስለ ጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ መመሪያውን ለማዘጋጀት በኤጀንሲዎች በኩል የቀረበ ሰነድ በመኖሩ ችግሩንም የሚያሳይ ጥናት መደረጉን እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም ይህን ለመሥራት የሚያስችል እቅድ ያቀደ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

58. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት ማሳደጊያና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ስለሚኖራቸው ግንኙነትና እና ትስስር ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ አለማዘጋጀቱ ተቋማት መከተል የሚገባቸውን ህግና ደንብ እንዳይከተሉ ከማድረግም ባሻገር በሥራ ግንኙነት በሚያገኙዋቸው የጉዲፈቻ ህፃናት ላይም አግባብነት የሌለው የጥቅም ትስስር ከመፍጠሩም ባሻገር የመብትና ደህንነት ጥሰት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

<u>***የጉዲፈቻ ህፃናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ የግንዛቤ ሥራ መሰራቱን በተመለከተ***</u>

59. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነትን በተመለከተ በህብረተሰቡ ላይ ግንዛቤ የሚፈጥር የሙያ አግባብነት ያለው ስልጠና ሊሰጥ እና ለህፃናት መብትና ደህንነት የሚቆም፣ የሚቆረቆር፣ ትብብርና አጋርነት ሊፈጥር የሚችል የህብረተሰብ ክፍል ሊፈጥር ይገባል፡፡

60. ሆኖም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባሉት ግዜያት ውስጥ የሰራውን የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መለካት በሚያስችል መልኩ በእያንዳንዱ በጀት ዓመት ቅደም ተከተል መሰረት በእስታትስቲካዊ አቀራረብ ሴ/ወ እና ድምር በሚል አቀማመጥ፤ እንዲሁም በሀገር ውስጥ በተሰጠው ግንዛቤ የመጡ ውጤቶችን የሚያሳይ ለህፃናት የተተገበሩ አማራጮችን ለማሳያ እስፖንሰርሺፕ፣ የመልሶ ወደ ቤተሰብ ማቀላቀል፣ ፎስተር ኬር እና የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ ያገኙ በሚል ከየክልሉ ዳታዎች በማሰባሰብ ያልሰራ መሆኑ ታውቋል፡፡

61. ስለ ሁኔታው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ግንዛቤ የተሰጠ መሆኑን፤እንዲሁም በሀገሮች የሚደረግ ጉዲፈቻ አገልግሎቱን ለሚፈልጉ ህፃናት ብቻ ተደራሽ እንዲሆን አሰራሮችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት በዚህ መሰረት የሀገር ውስጥ ድጋፉ እየጎለበተ የውጭ ጉዲፈቻ እየቀነሰ ያለበት ሁኔታ መኖሩን ፤ በተለይም በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናት ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የሚገኝ መሆኑን እና በውጭ አገር ጉዲፈቻ ላይ የህብረተሰቡ አመለካከት እየተቀየረ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

62. በተጨማሪም በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ድጋፍ እንክብካቤ፣በፎስተር ኬር፣ በአገር ውስጥ ጉዲፈቻ ዙሪያና በመልሶ ማቀላቀልና ማዋሃድ ዙሪያ ለ 226/ ሴ 100 እና ወ 126/ ተሳታፊዎች ስልጠና የሰጡ መሆናቸውን፣በተመሳሳይ ለ 2,113,218/ ወ 1,213,000 ሴ 900,218/ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መስራቱን በዚህም ምክንያት በማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ 1,654,085፣ በአገር ውስጥ ጉዲፈቻ 7,440 ህፃናት እንዲያድጉ፣16,452 በመልሶ ማዋሀድ ወደ ቤተሰቦቻቸው የተቀላቀሉ ሲሆን፤ ለ 3,010 ህፃናት የአደራ ቤተሰብ እየተፈለገላቸው ያለ መሆኑን፤

63. እንዲሁም ከፓክት ኢትዮጵያ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች አንድ ላይ በመሆን በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች 500,000 ለሚሆኑ ወላጅ ላጡና ለችግር ለተጋለጡ ህፃናት በማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ እንዲያገኙ በመደረግ ላይ መሆኑንና ፤ በተጨማሪም 164,115 ህፃናት አስፈላጊው ድጋፍና እንክብካቤ እየተደረገላቸው መሆኑን ፤ እንዲሁም ከየመን፣ ከሳውዲ አረቢያ እና ከሊቢያ የተመለሱ ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር መልሶ የመቀላቀል ሥራ የተሰራ በመሆኑ ከየመን 567 ህፃናት/ ወ 544፣ ሴ 23/፣ ከሳውዲ አረቢያ 632 ህፃናት/ ወ 423፣ ሴ 209/፤ እና ከሊቢያ 6 ሴት ህፃናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር መልሶ የመቀላቀል ሥራ በመሰራቱ በአጠቃላይ በማህበረሰብ አቀፍ የህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ ለ 4.6 ሚሊዮን ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

64. ጉዳዩ የቀረበላቸው ኃላፊ ይህን ቢሉም በመደበኛ /ፎርማል/ አሰራር ደረጃ ዳታዎችን ከየክልሉ በማሰባሰብ ለምን ያህሉ ግንዛቤ እንደ ተሰጠና በየክልሉ ምንስ ተጨባጭ ውጤት እንዳመጣ በሚያሳይ ሁኔታ የሰጡት መልስ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ መቀበል ያስቸግራል፡፡

65. ሆኖም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተትላቸው በአቀረቡት ሀሳብ ውስጥ በመደበኛነት ሁል ጊዜ ግምገማ ባያከናውኑም አልፎ አልፎ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራው ያመጣውን ለውጥ ለመገምገም የሞከሩ መሆናቸውን ገልፀው ተከታታይነት ባለው ሁኔታ እንዲፈፀም የተሰጠውን ምክረ ሀሳብ የሚቀበሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

66. የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች የሚሰሩት ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው በመሆኑ የተሰራው የግንዛቤ ሥራ ክልሎችን በማሳያነት በሚያመለክት እስታትስቲካዊ አቀራረብ /ወ፣ሴ እና ድምር የተገለፁትን ውጤቶች በሚለካ አኳኋን የማይቀርብ ከሆነ ቁጥሮችን ብቻ በማመልከት መግለፁ ገንዘብን፣ የሰው ሃይል እና ግዜን አለአግባብ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከማድረጉም ባሻገር ለብክነት በር ይከፍታል፡፡

## ወደ ውጭ በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናት የጉብኝት ክትትልን በተመለከተ

67. ህፃናት በጉዲፈቻ ወደ ውጭ ሀገር ከሄዱ በኋላ ደህንነታቸው መጠበቁን እና የጉዲፈቻ ተጠቃሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ህፃናቱ ባሉበት አገራት በአካል በመገኘት ጉብኝት ማድረግ፣ የጉብኝቱን ዝርዝር ሪፖርት ማቅረብ፤ እንዲሁም ባቀረቡት ሪፖርት መሰረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድና ግብረ-መልስ ሊሰጡ ይገባል፡፡

68. ይሁን እንጂ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባሉት ግዜያት ውስጥ በናሙና ተመርጠው በታዩት የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቶች አማካኝነት ማለትም በአሜሪካ ወርልድ የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅት ወደ አሜሪካ፣ በኩዊን ኦፍ ሜርሲ ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅት ወደ ፈረንሳይ፣ በቢታኒ ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅት ወደ አሜሪካ እና በአሶሴሽን ኦፍ መንዲ አዶፕታ ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅት አማካኝነት ወደ እስፔይን ጉብኝት ማድረጋቸው የተገለፀ ቢሆንም በሄዱባቸው አገሮች ስላገኙአቸው ህፃናት ሁኔታ ሪፖርት ያላቀረቡና ግብረ-መልስም ያልሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

69. ጉዳዩን በሚመለከት ጉብኝቱን በማዘጋጀት ተሳታፊ ለሆኑ በናሙና ለተመረጡ 4ት የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቶች በኦዲት ቡድኑ ከጉብኝት በኋላ ግብረ-መልስ የተሰጣቸው ስለመሆኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ሁሉም ያልተሰጣቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

70. ስለ ሁኔታው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ በ 05/05/ 08 ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በደፈናው የለም የሚል ሲሆን ፣ ለሁለተኛ ግዜ በ 17/06/08 ምክንያቱን በማስረጃ አስደግፈው እንዲገልፁ በተጠየቁበት ወቅት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከክልል፣ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተውጣጡ ከፍተኛ ኃላፊዎች በጣሊያንና በአሜሪካን አገር በተለያዩ ግዛቶች ጉብኝት ያደረጉ መሆኑ፤

71. ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግስት፣የክልል አካላት የተውጣጣ ቡድን በአሜሪካና ካናዳ በ 2006 ዓ.ም በአምስት ቡድን በመከፋፈል መጎብኘታቸውን፤ እንዲሁም ከ 2005- 2007 ዓ.ም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከተው የሥራ ሂደት ኃላፊና ባለሙያዎች በስፔይን፣ ጣሊያን ፣ ስዊድንና ቤልጀም ጉብኝት ማድረጋቸውን አመልክተው ከዚህ ጋር በተያያዘ የጠራ መረጃ በመያዝ በኩል መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች እንዳሉ መገንዘብ የቻሉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

72. የህፃናትን መብትና ደህንነት እና ያሉበትን ሁኔታ ለመከታተል የሚል ታላቅ አደራ ይዞ ውጭ ሃገር ድረስ ተሄዶ ያለ መረጃዎች መመለሱ የሀገር ሀብትን አግባብነት በሌለው የጉዞ ወጪ እንዲባክን ያደርጋል ፡፡

73. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በሪፖርቱ እንዲካተት በሰጡት ሀሳብ በጉዲፈቻ ወደ ውጭ ሀገር የሄዱ ህፃናትን የመጎብኘቱና ከጉብኝቱ በኋላ ሪፖርት ማቅረብና ግብረ መልስ ያለመስጠቱ የሀገር ሀብት ያለ አግባብ እየባከነ እንደሆነ ለቀረበው ግኝት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ 2008 ዓ.ም ባዘጋጀው የመልካም አስተዳደር እቅድ እንደ አንድ የመልካም አስተዳደር ችግር የለየው መሆኑን አመልክተው የጉዞ ወጪን በተመለከተ ከኤጀንሲዎች ጋር በሚገባው የሥራ ስምምነት /Operational Agreement/ መሰረት በኤጀንሲው የሚሸፈን በመሆኑ የሀገር ሀብት እንደ ባከነ መቆጠሩ ተገቢ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

74. ሆኖም እንደ ኦዲት ቡድኑ ሀብት በገንዘብ ፣ በሰው ሃይል እና በግዜ ተመኖች የሚለካ በመሆኑ፤ ገንዘብን በተመለከተ በሀገር ውስጥ የሚገኙ ኤጀንሲዎችን ከውጭ ኃላፊዎቻቸውን አስተባብረው እንዲያቀርቡ የሚያስገድዱ በመሆኑ ለዚህም ሳወጡት ወጪ የግምገማው ማስረጃ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ፤ የሰው ሃይልን በተመለከተ መረጃ ለማይቀርብበት ጉዳይ ውጭ ድረስ በመሄድ በሀገር ውስጥ መሰራት የሚገባውን ሥራ ትቶ መኬዱ እና ግዜን በተመለከተ ተጨባጭ ማስረጃ ሳልመጣለት ጉዞ የሥራ ጊዜን ማባከን አላስፈላጊ የሀገር ሀብት ብክነት መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በአፅንዖት ይገልፃል፡፡

<u>በጉዲፈቻ ህፃናት ዙሪያ የሚሰሩ ሥራዎች ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ</u>

75. በጉዲፈቻ ህፃናት ዙሪያ የሚከናወኑ ሥራዎች በተቀናጀና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ ለማስፈፀም የሚያስችሉ የትብብርና የቅንጅት ሰነዶች ሊዘጋጁና ሊተገበሩ ይገባል፡፡

76. ሆኖም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዲፈቻ ህፃናትን በሚመለከት የሚሰሩ የተለያዩ ድርጅቶች መኖራቸው ቢገለፅም የትብብርና ቅንጅት ሰነዶች ተዘጋጅቶላቸው በገቡት ቃል መሰረት የሚሰሩ ስለመሆኑ ማስረጃዎች አለቀረቡም ፡፡

77. ስለ ጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በሁሉም ክልሎች የሚገኙ የማህበረሰብ ጥምረት ድርጅቶች፣ ዕድሮች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የተባበሩት መንግስታት የህፃናት መርጃ ድርጅት፣ ዩ ኤስ ኤዲ፣ ፓክት ኢትዮጵያ፣ ሴቭ ዘ ችልድረን፣ሌሎች ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች፣ የሴቶች የልማት ቡድን እና የሴቶች አደረጃጀቶች የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

78. ይሁን እንጂ ጉዳዩ የቀረበላቸው ኃላፊ ይህን ቢሉም፤ በሥራው የዘረዘሩአቸው አካላት ሴቭ ዘ ችልድረን እና ፓክት ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤ እንዲሁም ክልሎች ከማህበረሰብ አቀፍ ተቋማት፣ አድሮችና ከሴቶች ልማት ቡድን ጋር ስለሚሰሩዋቸው ሥራዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተቋማቱ እንዲቋቋሙ ድጋፍ በመስጠት ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኝ መሆኑን ቢገልፁም

የትብብርና ቅንጅት ሰነድ ተዘጋጅቶላቸው የትብብር አሳታፊነትና ተጠያቂነት ባለው መንገድ ስለ መሥራታቸው የሚያመለክት ማስረጃ አልቀረበም፡፡

79. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ከተሰጡት ተግባራት የህፃናት መብትና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የሚመለከታቸውን አካላት ማስተባበር እና የሴቶች ህፃናትና ወጣቶችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች የማሰባሰብ ፣ የማደራጀት እንዲሁም በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቅ ያደርጋል ከሚለው አንፃር ያላቀረበ መሆኑ እንዲሁም ለማሳያ በአካባቢው ከሚገኘው ከአዲስ አበባ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ጋር በሀገር ውስጥ የሚደረግ ጉዲፈቻን በሚመለከት የግንዛቤ ሥራ ከመሥራት አኳያ የጥምረት ሥራ መሥራት ሲገባው ያልሰራ መሆኑ ከአዲስ አበባ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ በመገለፁ የቀረበውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል ፡፡

80. በጉዲፈቻ ህፃናት ዙሪያ የሚከናወኑ ሥራዎች በተቀናጀና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ ለማስፈፀም የሚያስችሉ የትብብርና የቅንጅት ሰነዶች አለመኖር ተጠያቂነት ያለው አሰራር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

<u>**የጉዲፈቻ ህፃናትን የሚመለከቱ መረጃዎች አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ**</u>

81. የጉዲፈቻ ህፃናትን የሚመለከቱ መረጃዎች መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት በማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም /Management Information System/ የተደገፈ ሊሆን ይገባል፡፡

82. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ በኦሮሚያ ክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳ ቢሮ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ፣የሀረሪ ክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳ ቢሮ፣ የድሬዳዋ መስተዳድር ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ እና የአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት ጉዳ ቢሮ መረጃዎችን በዳታ ቤዝ ሲስተም በተደራጀ መልኩ የማይዙ ሲሆን እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱም በኦዲቱ ወቅት እየተተገበረ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

83. ስለ ጉዳዩ በኦዲቱ በመስክ የታዩት የ5 ቱ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ፦

- ከኦሮሚያ ክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ የህፃናት መብትና ደህንነት ባለሙያ በዳታ ቤዝ ከሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የሚገናኙበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ፣
- ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ የህፃናት መብት ደህንነት ማስከበር ዋና የሥራ ሂደት ባለቤት በማኑዋል የተደራጀ አሰራር ቢኖርም በዳታ ቤዝ የመያዙ ሁኔታ የሌለ መሆኑን፣
- ከሀረሪ ክልል ሴቶችና ህፃናት ቢሮ የህፃናት ደህንነትና መብት እንክብካቤ ድጋፍ የሥራ ሂደት ባለቤት ከ 2004- 2007 ዓ.ም ድረስ ባለው ግዜ ውስጥ መረጃውን መያዝ እንኳ እንደሚገባቸው የማያውቁ መሆኑን፣

- በድሬዳዋ መስተዳደር ሴቶችና ሀፃናት ጉዳይ ቢሮ ባለሙያ የ አይ ቲ ባለሙያ የሌለ በመሆኑ በዳታ ቤዝ መረጃ መያዝ ያልጀመሩ መሆኑን፣
- እንዲሁም የአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ኦፊሰር በቢሮ ደረጃ የተደራጀ የዳታ ቤዝ ሲስተም አለመኖሩን አስታውቀዋል፡፡

84. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ወደ ፊት ይመሰረታል ተብሎ የታሰበበት ነው የሚል መልስ የሰጡ ሲሆን፤ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በክልሎች አማካኝነት የመረጃ ልውውጥ ተደራሽ ለማድረግ ጥረት የሚያደርግ መሆኑን፤ይህንንም ይበልጥ ለማቀላጠፍ የህፃናት ደህንነት ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም /Child Well-beng information System/ በተመረጡ ክልሎች ላይ በፓይለት ደረጃ እየተተገበረ የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
85. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊ ከላይ የተመለከተውን መልስ የሰጡ ቢሆንም የህፃናት ደህንነት ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም /Child Well-beng information System/ በተመረጡ ክልሎች ላይ በፓይለት ደረጃ እየተተገበረ ስለመሆኑና ፣መቼ እንደተጀመረ እና መቼ እንደሚጠናቀቅ ፣ በበጀት ደረጃ ምን ያህል እንደተያዘለት እና በአፈፃፀም እስከ አሁን ምን ያህል ወጪ እንደ ወጣ፤ እንዲሁም ለቀጣይ ውጤታማነቱ የክንውን ግምገማ /Performance Evaluation/ እየተደረገለት የሚገኝ ስለመሆኑ እና በማን ድርጅት እየተሰራ ስለመሆኑ የሚያሳይ አመላካች ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበለውም፡፡
86. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች የህፃናት ደህንነት መረጃ መረብ ዝርጋታን በተመለከተ በሪፖርት ውስጥ እንዲካተት በ 15/07/08 በላኩት መልስ በሴቭ ዘ ችልድረን እና በፓክት ኢትዮጵያ አጠቃላይ የፕሮጃክቱ ዋጋ ብር 10,381,764 በጀት የተመደበለት እ.ኤ.አ ጥቅምት 1/2013 ተጀምሮ ታህሳስ 31/2015 መጠናቀቅ አለበት የሚል ማስረጃ ቢያቀርቡም ተጠናቆ ርክክብ ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ ያላቀረቡ ሲሆን፤ በ 17/06/08 ለቀረበላቸው ምክንያት አዘል ጥያቄ የህፃናት ደህንነት ማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም ፓክት እና አፖዚት በተባሉ ድርጅቶች አማካኝነት በተፈፀመ ስምምነት በ 92 ሚሊዮን ዶላር መጀመሩን ፤ በተመሳሳይ ሁኔታም ህፃናትን የሚመለከቱ መረጃዎች የማደራጀቱ ሥራ ከ 1998 ዓ.ም ጀምሮ ስለ መደራጀቱ የተለያዩ መልሶች ማስረጃ ባልቀረበበት መልኩ ገልፀዋል፡፡
87. ይሁን እንጂ ከላይ የተገለፁት መልሶች በተጠናከረ ማስረጃ ያልተደገፉ እና ወጥነት የሌላቸው በመሆኑ ማለትም አንዱ በ 92 ሚሊዮን ዶላር ሌላኛው በ ብር 10,381,764 የሚሉ በመሆናቸው ለመቀበል አልተቻለም ፡፡

88. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች ጋር የመረጃ መረብ/ Child Well-beng information System/ ያልፈጠረ መሆኑ በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ህፃናትን መረጃ ልውውጥ ሂደት ወቅታዊና ተደራሽ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

**<u>በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ህፃናት ድህረ ጉዲፈቻ ክትትል /Post Placement / ሪፖርትን በተመለከተ</u>**

89. በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲ አማካኝነት ወደ ውጭ ሀገር ለሄዱ ህፃናት የላከው ድርጅት /ጉዲፈቻ አስፈፃሚው/ በወር፣ በስድስት ወር፣ በዓመትና ህፃኑ 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ በሚቀጥሉት ተከታታይ ዓመታት በየዓመቱ ሪፖርቱን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መላክ አለበት፤እንዲሁም ጉዲፈቻ ስለተደረጉ ህፃናት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርበው ቅጂ ህፃኑ በጉዲፈቻ እንዲሄድ ለተደረገበት ክልል፣ የህፃናት ጉዳይ ለሚመለከታቸው መ/ቤት እና ህፃኑን ለሰጠው ማሳደጊያ ድርጅት ሊሰጣቸው/ሊደርሳቸው ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው የታዩ የከተማ/ የክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች እና የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በሚከተለው ሁኔታ የተዘረዘሩት፡-

የከተማ/ የክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች

- የኦሮሚያ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ መረጃው የማይደርሰው መሆኑን፣
- በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ድህረ ጉዲፈቻ ሪፖርት በወቅቱና በስርዓቱ የማይደርሳቸው መሆኑ፣
- የሀረሪ ክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ መረጃው የማይደርሳቸው መሆኑ፣
- ድሬዳዋ መስተዳድር ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ መረጃው የማይደርሳቸው መሆኑ፣
- የአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት ጉዳ ቢሮ መረጃው የማይደርሳቸው መሆኑ
- የሰበታ ከተማ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ መረጃው የማይደርሳቸው መሆኑ የታወቀ ሲሆን፤

**በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥሎ የተመለከቱት በኦዲቱ በናሙና የታዩ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት፡-**

- ❖ ሀረሪ ክልል እንግዳ ህፃናት ማሳደጊያ IAG ከሚባል የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅት ጋር በሰራበት ወቅት እስከ 2006 ዓ.ም በተገቢው ሁኔታ ይደርሳቸው እንደነበር እና ድርጅቱ በመዘጋቱ የሪፖርቱ አመጣጥ መቀነሱን፣
- ❖ ድሬዳዋ ብርሃን ፋሚሊ ዌልፈር ፋውንዴሽን ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባሉት ግዜያት ድህረ ጉዲፈቻ ክትትል ሪፖርት ያልደረሳቸው መሆኑን፣
- ❖ በአዲስ አበባ ኪዳነ ምህረት /ካቶሊክ/ ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባሉት ግዜያት ድህረ ጉዲፈቻ ክትትል ሪፖርት ያልደረሳቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

91. በተጨማሪም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ገቢና ወጪ ከሆኑ ከሚከተሉት ደብዳቤዎች፡-

- የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑ አረጋዊት ቀደም ሲል በሚኒስትሩ ስር ሲተዳደር በነበረው የተሃድሶ ድርጅት በቋሚ ሠራተኝነት በሚያገለግሉበት ወቅት ድርጅቱ ልጆቻቸውን በአቅም ማነስ ምክንያት ማስተዳደር ስላልቻሉ ሁለት ልጆቻቸውን ተቀብሎ በስሩ በሚገኙ ማሣደጊያዎች ገብተው በመረዳት ላይ እያሉ አንዷን ልጅ በ1976 ዓ.ም. ለጉዲፈቻ ስዊድን አገር የተላከች በመሆኑና ወላጅ እናትዋ ልጃቸውን ለማግኘት ሲጠይቁ የት እንዳለች መረጃ ያለማግኘታቸው፣ በሚ/ር መ/ቤቱ ገቢና ወጪ ከሆኑ ደብዳቤዎች ፋይል የደብዳቤ ቁጥር ሴህወጉ16/1/16/01 በቀን 20/01/2006
- በደቡብ ክልል በተዘጉ ማሳደጊያዎች ከነበሩ ሕፃናት ውስጥ የጉዲፈቻ ቤተሰብ ያገኙትን 3 ሕፃናት ለ3ቱ ጣሊያን ዜጎች መሰጠታቸው ቢታወቅም ሆኖም ያሉበትን ሁኔታ የሚገልጽ ሪፖርት ያለመኖሩ፣ በሚ/ር መ/ቤቱ ገቢና ወጪ ከሆኑ ደብዳቤዎች ፋይል የደብዳቤ ቁጥር 11/211/253/04 በቀን 7/6/2004
- በደቡብ ክልል በክልል ደረጃ በተካሄደው ግምገማ ከእስታንዳርዱ በታች የሆኑ ተቋማት መገኘታቸውና እነዚሁ ተቋማት ከፌዴራል በጎ አድራጎትና ማሕበራት ኤጀንሲ ፈቃድ ወስደው አገልግሎት እየሰጡ ያልተገኙ ስድስት የሕፃናት ማሳደጊያዎች በግምገማው ወቅት በራሳቸው ጊዜ ዘግተው መገኘታቸው፣ በሚ/ር መ/ቤቱ ገቢና ወጪ ከሆኑ ደብዳቤዎች ፋይል የደብዳቤ ቁጥር ሴሕወጉ/00-1/71/2 በቀን 29/02/2006
- በደቡብ ክልል እስካሁን በሕፃት ዙሪያ የማይንቀሳቀስና የሥራ ግንኙነት የሌለው አዱናይ በተባለ የግብረሰናይ ድርጅት ከክልሉ መንግሥት ዕውቅና ውጭ በተጭበረበረ ሰነድ ሕገወጥ የውጭ ጉዲፈቻ ሲፈጽም መገኘቱ፣ በሚ/ር መ/ቤቱ ገቢና ወጪ ከሆኑ ደብዳቤዎች ፋይል የደብዳቤ ቁጥር ሴህወጉ9/945/1 በቀን 20/8/2006
- ኤድዋርድ በርተን እና ሜሎድ በርተን የተባሉ የአሜሪካ ቤተሰቦች በአዶኘሽን አድቮኬት ኢንተርናሽናል አማካኝነት በ1992 ዓ.ም. በ9 ዓመቷ በጉዲፈቻ የተወሰደች ሕፃን 2 ዓመት ከ3 ወር ቆይታ በኋላ በሕወት እንደሌለች ሪፖርት መደረጉ ፣ በመሆኑም ለሕፃኗ ሞት ምክንያቱ እና ስለ ሪፖርቱ መዘግየት፣ በሚ/ር መ/ቤቱ ገቢና ወጪ ከሆኑ ደብዳቤዎች ፋይል የደብዳቤ ቁጥር 11-110/145/05 በቀን 3/01/05

በኦዲቱ ወቅት ከደብዳቤዎቹ መረዳት የተቻለው በሚኒስቴር መ/ቤቱ የድህረ ጉዲፈቻ ሪፖርት ወቅታዊ ክትትል አለመደረግ ችግር መሆኑን ያመለክታል። ችግሩም በኦዲቱ ወቅት አለመፈታቱ ታውቋል።

92. ስለ ሁኔታው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የመረጃ ቅብብሎሽ ያለ መሆኑን ገልፀው ሰነዱ በጣም ብዙና ለብዙ ዓመታት የተከማቸ በመሆኑ መግለፅ የሚቸገሩ መሆኑን ፤ ነገር ግን አብዛኞቹ መረጃ ጠያቂዎች ምላሽ ያገኙ ቢሆንም፣ የ 1970 ዎቹን እና የ 1980 ዎቹን በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ህፃናትን መረጃ ያላገኙ አገልግሎት ጠያቂዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገልፀዋል።

93. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውጭ በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናትን መረጃዎች በዓመታት ቅደም ተከተል መሰረት በተደራጀ መልኩ በዳታ ቤዝ ሲስተም አለመያዙ ወደ ውጭ በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናት መረጃዎች ለሚፈልጉ ህብረተሰብ ክፍሎች ህፃናቱ ስላሉበት ሁኔታ እንዲከታተሉ መረጃ እንዲያጡና እንዲንገላቱ ከማድረጉም በላይ ህፃናቱም ስለ ሀገራቸው ክትትል በማድረግ በአደጉ ግዜ የቤተሰብ እና የትውልድ ሀገር ፍቅር እንዳይኖራቸው ያደርጋል።

<u>**በውጭ የሚገኙ ኢምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች የሚደረግ ክትትልን በተመለከተ**</u>

94. በውጭ ሀገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ኢምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ህፃናትን ሁኔታ የክትትልና የግምገማ ሥራ እንዲሰሩ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስምምነት ሊፈጥር ይገባል።

95. ሆኖም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ጉዳይ በማስተባበር በኩል የሥራ ድርሻው ከሆነው የመንግስት አካል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የገባውን ስምምነት የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ያላቀረበ በመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበበት ምክንያት ይገለፅ ተብሎ በተጠየቀበት ወቅት የመግባቢያ ሰነድ የቀረበ ሲሆን፤በቀረበው መግባቢያ ሰነድ ውስጥ የተጠቀሰው ዓላማ በየሁለት ዓመቱ ህፃናቱ ወደ ሄዱበት ሀገር በመሄድ በአካል መከታተል፤

96. እንዲሁም በየሀገራቱ በመሄድ ሁሉንም ማዳረስ የራሱ ውስንነት ያለው በመሆኑ በየሀገራቱ ያሉ ቆንስላ ጽ/ቤቶች የሥራቸው አካል በማድረግ የሄዱ ልጆችን መረጃ አግኝተው በቀጣይነት የክትትል ሥራውን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ /ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ ጋር በሚደረግ የመረጃና መረጃውን ተከትሎ በሚቀርብ የግበረ መልስ መስተጋብር መሰረት በመሥራት ክትትሉ ውጤታማ እንዲሆንና የህፃናቱንም ደህንነት በበለጠ ለመከታተል የሚያስችል ሆኖ የተዘጋጀ መሆኑ ተገልፆ፤ የሁለቱም ሚኒስቴር መ/ቤቶች ኃላፊነት በውስጡ ተካቶ ቀርቧል።

97. የሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን ኃላፊነት በተመለከተ በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናትን የተመለከቱ መረጃዎችን የህፃናቱን ስም ዝርዝር፣ ህፃናቱ የተወሰዱበትን ሀገር ስም ፣ ህፃናቱን የወሰደውን የጉዲፈቻ ኤጀንሲ ስም እና አድራሻ እየለየ መስጠት እና የውጭ ጉዳይ በሰጠው ግብረ መልስ መሰረት በጉዲፈቻ ሂደት ያሉ ክፍተቶችን እና አሰራሮችን ማሻሻልና እርምጃ ለመውሰድ የሚቻለውን በመለየት እርምጃ መውሰድ የሚል  በሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴርና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በ 15/06/05 የተፈረመ የመግባቢያ ሰነድ ያለ ሲሆን፤

98. አተገባበሩን በተመለከተ በናሙናነት ከቀረቡ ማስረጃዎች ለማሳያነት ህዳር 4/2006  ለአሜሪካ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አዲስ አበባ ፡- በዘንድሮ በጀት ዓመት በተያዘ እቅድ ውስጥ በጉዲፈቻ የኢትዮጵያ ህፃናትን የሚያሳድጉ አሜሪካውያን ወላጆችን በተለያዩ የገፅታ ግንባታ ሥራዎች ላይ እንዲያግዙን የሚያስችል በመሆኑ የወላጆቹ መረጃ/ስም፣ አድራሻ፣ ቴሌፎን፣ ወዘተ/ የሚመለከተው አካል ተጠይቆ እንዲላክልን የሚል በመሆኑ ፡፡ ይህ ሀሳብ የሚያመለክተው ህፃናቱን የሚያሳድጉ ግለሰቦችን ለሀገር ገፅታ ግንባታ መፈለጋቸውን የሚያመለክት እንጂ የተገባውን ስምምነት የማያንፀባርቅ በመሆኑ በማስረጃነት ሊቀረብ አይችልም ፡፡

99. ስለ ጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ የመስሪያ ቤቱ ኃላፊዎችና የክልል ባለስልጣናት በየግዜው እየሄዱ ክትትል ያደረጉበት ሁኔታ ያለ ሲሆን፤ በተጨማሪም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናት ለኢትዮጵያ ኢምባሲዎች እንዲደርስ የመረጃ ልውውጥ የሚያደርጉ መሆኑን፤ የመረጃ ልውውጡም የህፃናቱን እድሜ፣ ፆታና የት ሀገር እንደሄዱ በሚያመለክት መልኩ በመሆኑ ለኢምባሲዎቻችን በሚያመች ሁኔታ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

100. ኃላፊው በሰጡት መልስ ይህን ይበሉ እንጂ በመግባቢያ ሰነዱ የተገለፀው የሴቶች፣ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርን ኃላፊነት በተመለከተ በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናትን የተመለከቱ መረጃዎችን የህፃናቱን ስም ዝርዝር፣ ህፃናቱ የተወሰዱበትን ሀገር ስም፣ህፃናቱን የወሰደውን የጉዲፈቻ ኤጀንሲ ስም እና አድራሻ እየለየ መስጠት እና የውጭ ጉዳይ በሰጠው ግብረ መልስ መሰረት በጉዲፈቻ ሂደት ያሉ ክፍተቶችን እና አሰራሮችን ማሻሻልና እርምጃ ለመውሰድ የሚቻለውን በመለየት እርምጃ መውሰድ የሚል በመሆኑ ስምምነቱ በ 2005 ዓ.ም ከፀደቀ

ጀምሮ ስለ ህፃናቱ ሁኔታ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት ውጭ ላሉ ቆንስላ ጽ/በቶች ማስረጃ ተልኮላቸው ለህፃናቱ ያደረጉትን ክትትል እና የአሰራር ክፍተቶች ስለመኖራቸውና አለመኖራቸው የሚሳይ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

101. በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ህፃናትን መረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት በውጭ ለሚገኙ የኢትዮጵያ ኢምባሲ እና ቆንስላ ጽ/ቤቶች በማድረስ 18 ዓመት እስኪሞላቸው ግዜ ድረስ ስላሉበት ሁኔታ ክትትል በማድረግ የሀገርና የወገን ፍቅር ኖሯቸው እንዲያድጉ አለመደረጉ ህፃናቱ ባዕድ አመለካከት እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ ሀገርና ወገን ከነሱ ማግኘት የሚገባቸውን የዕውቀት፣የቴክኖሎጂ፣ ኢንቨስትመንትና የመሳሰሉትን እንዲታጣ ያደርጋል፡፡

**<u>የሴክተር መ/ቤቶች የህፃናት ጉዳይን በዕቅድና ፕሮግራሞቻቸው አካተው መንቀሳቀሳቸውን በተመለከተ</u>**

102. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች የህፃናትን ጉዳይ በእቅድና ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ አካተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለመደገፍና ለመከታተል የሚረዳ ቼክሊስት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

102 ሆኖም በኦዲቱ ወቅት ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችና ከሀረሪ ክልል የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች መረጃ መረዳት የተቻለው ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባሉት ግዜያት ውስጥ ያልተሰራ መሆኑና በ 2008 ዓ.ም እንቅስቃሴው በከፍተኛ ደረጃ የተጀመረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

103 እንዲሁም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተደረገው ክትትልና ድጋፍ ሪፖርት በሴክተር መ/ቤቶች ላይ የታዩ ችግሮች:-

- ❖ ክትትል በተካሄደባቸው አብዛኛው ሴክተሮች በሕፃናት ዙሪያ የታቀዱ ዕቅዶች የ2006 በጀት ዓመት አፈጻጸም ትንተናን መነሻ በማድረግ እንዲሁም የሕፃናት ጉዳይ የትኩረት ነጥቦች፣ አላማ፣ ግብ፣ መነሻ ኢላማና ውጤት አመላካች ፣ የማስፈጸሚያ ስልቶችን ያካተቱ አለመሆናቸው፣ /በተመረጡ 14 ፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶች የሕፃናት ጉዳይ በ2ኛ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ተካቶ እንዲታቀድ ከትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ለመስጠት የተደረገው የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት ታህሣሥ 2007 ዓ.ም/ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሕፃናትን ጉዳይ የማስፈጸም ኃላፊነት የተጣለባቸው መሆኑና ግዴታ እንዳለባቸው ሳይሆን ይህፃናትን ጉዳይ ማስፈፀም እንደተጨማሪ ሥራ አድርጎ የመመልከት ሁኔታ ጎልቶ የሚታይ መሆኑ፣

/በተመረጡ 14 ፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶች የሕፃናት ጉዳይ በ2ኛ የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተካቶ እንዲታቀድ ከትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ለመስጠት የተደረገው የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት ታህሣሥ/ 2007 ዓ.ም/

- ❖ ክትትል ከተካሄደባቸው 14 ሴክተሮች መካከል በ10ሩ በዕቅድ ተይዘው በሕፃናት ዙሪያ የሚከናወኑ እቅዶች ቢኖሩም በ7ቱ መ/ቤቶች ለሕፃናት ተለይቶ የማስፈፀሚያ በጀት ባለመመደቡ ሥራዎችን ለማከናወን አለመቻሉ፣
- ❖ በተመረጡ 14 ፌዴራል ሴክተር መ/ቤቶች የሕፃናት ጉዳይ በ2ኛ ዕ.ት.ዕ ተካቶ እንዲታቀድ ከትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ለመስጠት የተደረገው የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት ታህሣሥ/ 2007 ዓ.ም/

  ሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግሮችን የለየ ቢሆንም ችግሮቹ መቀረፋቸውን ለማረጋገጥ በቼክ ሊስት በተደገፈ ሁኔታ የሰራቸው የቁጥጥርና ክትትል፣እንዲሁም የማስተካከያ እርምጃዎች አመላካች ማስረጃዎች በኦዲቱ ወቅት ያልቀረቡ መሆኑ መረዳት ተችሏል፡፡

104. ስለ ጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ አሰራሮችና መመሪያዎችን በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በመሥራት የሀገር ውስጥ ድጋፍ እንዲጎለብት በማድረግ ችግሮች እየቀነሱ እንዲሄዱ ማድረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

105. የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች የህፃናትን ጉዳይ በእቅዶቻቸውና በፕሮግራማቸው አካተው መስራታቸውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመከታተሉና ተግባራዊ በማያደርጉ ላይ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰዱ ህፃናትን በሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ ለማሳደግ የሚፈልጉ ዜጎች ግንዛቤው እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በላይ መንግስት ህፃናት በሀገራቸው የማደግ እድል እንዲኖራቸው ያቀደው እቅድ እንዳይሳካ ተፅእኖ ሊፈጥር ይችላል ፡፡

**<u>ከሀገር ውጭ ጉዲፈቻ የተደረጉ ህፃናት መረጃ በተሟላ ሁኔታ ስለመያዙ ክትትል መደረጉን በተመለከተ</u>**

106 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሮች መካከል የሚደረግ የጉዲፈቻ ህፃናት መረጃዎችን ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች እና የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በተሟላ መልኩ መያዛቸውን ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

107 ሆኖም በናሙና ተመርጠው በመስክ ኦዲት በታዩት በሰበታ ብርሃን ፋሚሊ ዌል ፌር ፋውንዴሽን፣ ገላን ኤስ ኦ ኤስ የህፃናት ማሳደጊያ፣ሀዋሳ አጁጃ ህፃናት ማሳደጊያ፣ ሀረሪ ክልል እንግዳ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋም፣ ድሬዳዋ ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን፣ ድሬዳዋ አቤነዘር ህፃናት ማሳደጊያ፣ አዲስ አበባ ኤስ ኦ ኤስ ትኩል ህፃናት ማሳደጊያ፣አዲስ አበባ

ብርሃን ፋሚሊ ፋውንዴሽን፣ አዲስ አበባ ኪዳነ ምህረት/ካቶሊክ/ ህፃናት ማሳደጊያ እና አዲስ አበባ እድገት የህፃናት ማሰደጊያ ስለ መረጃ አያያዝ አቅም ማጎልበት በትምህርት መልክ ያልተሰጣቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

108 ስለ ሁኔታው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ግንዛቤና የእርምት እርምጃ በየግዜው የሚደረግ መሆኑን እና በተጨማሪም ከተቋማት ጋር የጋራ ውይይት የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

109 ኃላፊው ይህን መልስ ይስጡ እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ግንቦት /2000/ ዓ.ም በተዘጋጀ በሀገሮች መካከል የሚደረግ የጉዲፈቻ አገልግሎት አሰጣጥ የውስጥ አሰራር መመሪያ ላይ በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናትን በተመለከተ የህፃናት ማሳደጊያውን እና የላኪውን የጉዲፈቻ አስፈፃሚውን ድርጅት መረጃዎች በተሟላ መልኩ ስለመያዛቸው ክትትል ያደርጋል፡፡ የመረጃ አያያዛቸውንም ያጎለብታል የሚል በመሆኑ ይህን ስለ መስራቱ በማስረጃ ተደግፎ ባለመቅረቡ የተሰጠው መልስ ተቀባይነት የለውም፡፡

110 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዲፈቻ ህፃናት መረጃዎችን ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች እና የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በተሟላ መልኩ እንዲይዙ ክትትል አለማድረጉና የአቅም ማጎልበት ሥራ በ አይ ቲ የተደገፈ ስልጠና አለመስጠቱ በመረጃዎች መጥፋት ምክንያት አገልግሎት ጠያቂ የህፃናት ቤተሰቦች ለእንግልት እንዲዳረጉ ያደርጋል፡፡

<u>ለውጭ ጉዲፈቻ ብቁ የተባሉ በሀገር ውስጥ አመራጭ ያላገኙ ህፃናትን በተመለከተ</u>

111. በሀገሮች መካከል በሚደረግ ጉዲፈቻ ብቁ ሆነው የተመረጡ ሕፃናት በሀገር ውስጥ በሚደረግ ድጋፍና ክብካቤ እንዲያድጉ ለማድረግ የተወሰደው እርምጃ ሊሳካ ያልቻለበት ምክንያትና ለውጭጉዲፈቻ እንዲሰጥ የመጨረሻውን ውሳኔ የሰጠው አካል አስተያየት በዝርዝር ሊቀርብ ይገባል፡፡

112. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩ የክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች፡-

- የኦሮሚያ ክልል ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ህፃናት በሀገር ውስጥ የማደግ እድል እንዲያገኙ በዞን፣ወረዳ እና ከተማ ደረጃ ሙከራዎች አድርጎ የውጭ እድል ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን፣
- የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በ 2005 ዓ.ም የውጭ ጉዲፈቻ ቢያቆሙም፤ በጤና ችግር ምክንያት በሀገር ውስጥ መታከም የማይችሉ በህክምና ቦርድ የተረጋገጠላቸውን ህፃናት ብቻ የውጭ እድል ተጠቃሚ በማድረግ ለተቀሩት በአካባቢው

- ❖ ህብረተሰብ የማህበረሰብ አቀፍና የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየሰሩ መሆናቸውን፣
- ❖ በአዲስ አበባ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋም አንድ ህፃን ለውጭ ሀገር ጉዲፈቻ ብቁ ነው ብሎ የሚፅፍላቸውን ማመልከቻና ተያያዥ ማስረጃዎች በማጣራት ብቃቱን/ አለመብቃቱን የሚያረጋግጥ መሆኑን ታውቋል፡፡

113. በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ በየክልሉ መረዳት የቻለው ህፃናት ለውጭ ጉዲፈቻ ብቁ ናቸው ተብለው ማረጋገጫ የሚሰጣቸው በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ ተሞክሮ ሲሆን፤ በሀገር ውስጥ በሚገኙ ሌሎች አጎራባች ክልሎች በጋዜጣም ሆነ በአማራጭ መገናኛ ዘዴዎች በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ እድሉ ሳይፈለግላቸው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

114. ስለ ሁኔታው በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለ ህፃናት መብት ማስከበር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በክልሎች ሌሎች አማራጭ እንዳልተገኘላቸውና በውጭ ጉዲፈቻ እንዲረዱ የሚጠየቅበት ደብዳቤ ሲቀርብ፤ ይህም ማለት ሌሎች አማራጮች በሀገር ውስጥ ያልተገኙ መሆኑን እና በሀገሮች መካከል ለሚደረግ ጉዲፈቻ ብቁ መሆኑን ባረጋገጡት መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያፀደቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

115. ኃላፊው ከላይ የተገለፀውን መልስ ቢሰጡም ከማስረጃዎች መረዳት የተቻለው ህፃናት በአካባቢያቸው በሚገኙበት ክልል ብቻ አማራጮች እየተሞከሩላቸው በሀገር ውስጥ አማራጭ አልተገኘላቸውም እየተባለ ወደ ውጭ የሚላኩ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ መቀበል ያስቸግራል፡፡

116. ህፃናት በሀገራቸው በሚያውቁት ህብረተሰብ ውስጥ እንዲያድጉ አማራጮችን ሁሉ መጠቀም አለመቻሉ ህፃናት በማያውቁት ህብረተሰብ ውስጥ የስነ-ልቦና ተፅኖና የማንነት ጭንቀት እንዲያድርባቸው ያደርጋል፡፡

**<u>በኦዲቱ ወቅት በመልካም ተሞክሮ የታዩ ተቋማትን በተመለከተ</u>**

117. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል አቤነዘር ስፖርቲንግ ዴቨሎፕመንት ህፃናት ማሳደጊያ ተቋም በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት 16 ሴት  እና 30 ወንዶችን በድምሩ 46 ህፃናት አብዛኛው የጤና ችግር ያለባቸውን እና በሚዛን ተፈሪ ቤንች ማጂ ዞን በጎጂ ባህል ሚንጌ/ ህፃናት የፊት ጥርስ አውጥተው ከተወለዱ ዘር ያጠፋሉ/ ተብሎ ከሚታሰብ አካባቢ የተገኙ ብዛታቸው 20 የሆኑ ልጆችን ትምህርት አስገብቶ የሚያስተምር መሆኑ፤ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

118. እንዲሁም በድሬዳዋ መስተዳድር ከሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ ጋር ፖዘቲቭ አክሽን ፎር ዴቨሎፕመንት የተባለ ግብረሰናይ ድርጅት የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻን ለማጠናከር  በከፍተኛ ሁኔታ ለህብረተሰቡ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በመሥራት የአካባቢው ኗሪ  ብዛታቸው 39 ህፃናትን በሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ ተጠቃሚ በማድረግ ህፃናቱ  በጥሩ ሁኔታ በሚያውቁት ማህበረሰብ እንዲያድጉ ማድረጉ በመስክ ኦዲቱ ታውቋል፡፡

<u>ማስገንዘቢያ</u> ፡- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኦዲቱ መውጫ ስብሰባ ወቅት በኦዲቱ ሂደት የታዩትን ክፍተቶች እንደግብዓት በመውሰድ አዲስ በተዘጋጀ ያልፀደቀ በአገሮች መካከል የሚደረግ የጉዲፈቻ አፈፃፀም ረቂቅ መመሪያ ታህሳስ 2008 ዓ.ም ውስጥ የሚከተሉትን በማካታት የሚከታተል መሆኑ ተገልጿል፡፡ እነርሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

ክትትል፣ ግምገማ እና የመረጃ አያያዝ ስርዓትን በተመለከተ

ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-

1. የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቶች ወይም ህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በተቀመጠላቸው እስታንዳርድ መሰረት እየሰሩ ስለመሆናቸው የህፃናትን መብትና ደህንነት ያስጠብቃሉ ብሎ ባመነበት መንገድ ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግ መሆኑን፣
2. የድህረ ጉዲፈቻ ሪፖርት እንዲቀርብለት በማድረግ ወይም በኢንስፔክሽን ጉዲፈቻ አስፈፃሚው ኤጀንሲው ወይም ህፃናት ማሳደጊያ ተቋሙ ድረስ በግንበር በመሄድ ክትትል ማድረግ የሚገባውና የሚችል መሆኑን፣
3. ከጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቶች ጋር በሚገባው የሥራ ስምምነት መሰረት በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናት መብትና ደህንነት መጠበቁን ለማረጋገጥ ህፃናቱ ያሉበት ሀገር በአካል በመገኘት ጉብኝት ለማድረግ የሚያስችል እቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ እና

4. ህፃናቱን በግንባር ሄዶ የተመለከተ ግብረ ሃይል በተመለሰ በ 15 ቀናት ውስጥ ሪፖርቱን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ያለበት መሆኑን፣
5. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቶች፣ በህፃናት ማሳደጊያ ተቋማትና የህፃናትን መብትና ደህንነት ለመከታተል በተቋቋመው ዳይሬክቶሬት ውስጥ የድህረ ጉዲፈቻ ሪፖርት በአግባቡ መደራጀቱን የሚቆጣጠርና የሚከታተል መሆኑን፣
6. በጉዲፈቻ የሄዱ ህፃናትን በተመለከተ የህፃናት ማሳደጊያ ተቋሙና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቱ ስለላኳቸው ህፃናት የተሟላ ማስረጃ ስለመያዛቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትል የሚያደርግ መሆኑን፣

   በሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናትን መብትና ደህንነት ለመከታተል የሚቋቋሙ የሥራ ሂደቶች ተግባርና ሃላፊነትን ከሚመለከቱ ውስጥ

   1. በሀገሮች መካከል በሚደረግ የጉዲፈቻ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናትን መረጃ በተደራጀ የመረጃ ቋት መግባቱን ማረጋገጥ፣
   2. በሀገሮች መካከል በሚደረግ የጉዲፈቻ አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ህፃናትን የድህረ ጉዲፈቻ ሪፖርቶች እንዲቀርቡ ክትትል ማድረግና ለክልሎች መረጃዎቹን ማሰራጨት፣
   3. በህፃናት ማሳደጊያ ተቋማትና በጉዲፈቻ አስፈፃሚ ድርጅቶች ላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ማከናወን፤ ጉድለቶች ተፈጽመው ከተገኙ አስፈላጊው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በህፃናት የድጋፍ አገልግሎትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ጥር 2008 ዓ.ም ባልፀደቀ ረቂቅ ውስጥ ክትትል ስለሚያደርግባቸው ጉዳዮች ከተካተቱት ውስጥ ከኦዲቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

1. ህፃናትን በተመለከተ በሚመለከታቸው አካላት ፀድቀው ወደ ሥራ የገቡ ፕሮጀክቶችን በዓላማቸው መሰረት መሰራታቸውን ለማረጋገጥ ፕሮጀክቶች በስታንዳርድ መሰረት መሰራታቸውን የማረጋገጥ ሥራ መሥራት፣
2. ህፃናትን በተመለከተ የተጠኑ ጥናቶች ህፃናትን በሚጠቅም መልኩ ተግባራዊ እንዲሆኑ ክትትል ማድረግ፣

3. በጉዲፈቻ አስፈፃሚና በህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት መካከል ያልተገባ ግንኙነትን መስበር፣
4. በህፃናት ማሳደጊያዎች የሚገኙ ህፃናት በስታንዳርድ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት እያገኙ መሆናቸውን መከታተልና መደገፍ፣
5. የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በተቋቋሙበት ዓላማ አንፃር መተግበራቸውን ማረጋገጥ፣
6. የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በአማራጭ የህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ እንዲሰሩ ማበረታታት፣ የሚሉት ከኦዲቱ ጋር በተያያዥነት ታይተው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደፊት የሚሰራቸው ስለ መሆኑ ከላይ የተገለፁትን ሁለት መመሪያዎች በማቅረብ በረቂቅ ሪፖርቱ ውስጥ ታሳቢ ሆነው እንዲታዩ በመውጫ ስብሰባ ወቅት ቢጠይቅም በአሁኑ ወቅት በረቂቅነት ያሉና ያልፀደቁ በመሆናቸው፤ ሆኖም ግን በኦዲቱ ሂደት ውስጥ የታዩት እነዚህ ክፍተቶች ትኩረት እንዲያገኙ መደረጋቸው የሚበረታታ መልካም ጅምር መሆናቸውን ከግናዛቤ በማስገባት፤ የወደፊት አተገባበራቸውን በተመለከተ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በሚቀጥሉት ዓመታት በሚያደርገው የክትትል ኦዲት የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሀሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው የጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነት አጠባበቅ ስርዓት ክትትልና አፈፃፀምን በተመለከተ በናሙና በኦዲቱ ተመርጠው በታዩት የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር፣የክልልና የከተማ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ቢሮዎች፤እንዲሁም የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች የሚከተሉት መደምደሚያዎች ተሰጥተዋል፡፡

119. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት መብትና ደህንነት የሚያስጠብቅ በ ሚያዚያ 2003 ዓ.ም የመጨረሻ ብሔራዊ ረቂቅ የህፃናት ፓሊሲን አዘጋጅቶ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ ያላፀደቀ መሆኑ፤ ብሄራዊ የህፃናት ፖሊሲው ባለመፅደቁ ምክንያት ለ 1.5 ሚሊዮን ህዝብ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ለመስጠት ታቅዶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

120. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ መመሪያዎች ለሚመለከታቸው የሕፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በተሟላ ሁኔታ ተሰራጭተው ያልተገኙ መሆኑ፣

121. በሁሉም የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት የህፃናት አቀባበልና ምደባን በተመለከተ ወጥ የሆነ መመሪያ እና አሰራር ስርዓት ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ወላጆቻቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ያጡና ለችግር የተጋለጡ ህፃናትን መምረጫ መመሪያ/የካቲት 2002 ዓ.ም/ መሰረት አድርጎ የማይከናወን መሆኑ፣

122. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እና ከጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ለሚቀርብለት የሩብ ዓመት ሪፖርትን መሰረት በማድረግ ለሚያቀርቡት ዓመታዊ ሪፖርት እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው የህፃናት ማሳደጊያ እና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች መገምገሚያ ቼክሊስቶች መሰረት ግምገማ ለተደረገላቸው ግብረ-መልስ የማይሰጥ እና በተዋረድ ያሉትንም አካላት ግብረ-መልስ የመስጠት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያላደረገ መሆኑ፣

123. የህፃናት ማሳደጊያና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ስለሚኖራቸው ግንኙነትና እና ትስስር ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣

124. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነትን በተመለከተ በህብረተሰቡ ላይ ግንዛቤ የሚፈጥር የሙያ አግባብነት ያለው ስልጠና መሰጠቱን በተመለከተ በ ከ 2004- 2007 ዓ.ም ባሉት ግዜያት ውስጥ መለካት በሚያስችል መልኩ በእያንዳንዱ ዓ.ም ቅደም ተከተል መሰረት በእስታትስቲካዊ አቀራረብ ሴ/ወ እና ድምር በሚል አቀማመጥ፤ እንዲሁም

125. በተሰጠው ግንዛቤ መሰረት በሀገር ውስጥ የመጡ ውጤቶችን የሚያሳይ ለህፃናት የተተገበሩ አማራጮችን ለማሳያ እስፖንሰርሺፕ፣ የመልሶ ወደ ቤተሰብ ማቀላቀል፣ ፎስተር ኬር እና የሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ ያገኙ በሚል ከየክልሉ ዳታዎች በማሰባሰብ ያልሰራ መሆኑ፣

126. ህፃናት በጉዲፈቻ ወደ ውጭ ሀገር ከሄዱ በኋላ ደህንነታቸው መጠበቁን እና የጉዲፈቻ ተጠቃሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ህፃናቱ ባሉበት አገራት በአካል በመገኘት ጉብኝት አድርገው የጉብኝቱን ዝርዝር ሪፖርት ያላቀረቡና ግብረ-መልስ ያልሰጡ መሆኑ፣

127. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዲፈቻ ህፃናትን በሚመለከት የሚሰሩ የተለያዩ ድርጅቶች መኖራቸው ቢገለፅም የትብብርና ቅንጅት ሰነዶች ተዘጋጅቶላቸው በገቡት ቃል መሰረት የሚሰሩ ስለመሆኑ ማስረጃዎች ያልቀረቡ መሆኑ፣

128. የጉዲፈቻ ህፃናትን የሚመለከቱ መረጃዎች መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት በማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም /Management Information System/ የተደገፈ አለመሆኑ፣

129. በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲ አማካኝነት ወደ ውጭ ሀገር ለሄዱ ህፃናት የላከው ድርጅት/ጉዲፈቻ አስፈፃሚው/ በወር፣ በስድስት ወር፣ በዓመትና ህፃኑ 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ በተከታታይ ዓመታት በየዓመቱ ሪፖርቱን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መላክ አለበት፤እንዲሁም ጉዲፈቻ ስለተደረጉ ህፃናት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርበው ቅጺ ህፃኑ በጉዲፈቻ እንዲሄድ ለተደረገበት ክልል መድረስ እንዳለበት የታወቀና፣ የህፃናት ጉዳይ ለሚመለከታቸው መ/ቤት እና ህፃኑን ለሰጠው ማሳደጊያ ድርጅቶች እንዲደርሳቸው መደረግ ሲገባው የማይደርሳቸው መሆኑ፣

130. በውጭ ሀገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ኢምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ህፃናትን ሁኔታ የክትትልና የግምገማ ሥራ እንዲሰሩ ከሚመለከተው የመንግስት አካል

131. ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር የገባውን ስምምነት የሚያሳይ ማስረጃ የቀረበ ቢሆንም ከ 2005 ዓ.ም ጀምሮ በቆንስላ ጽ/ቤቶቹ የተደረገውን ክትትል የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

132. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች የህፃናትን ጉዳይ በእቅድና ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ አካተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለመደገፍና ለመከታተል የሚረዳ ቼክሊስት ያላዘጋጀ መሆኑ፣

133. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሮች መካከል የሚደረግ የጉዲፈቻ ህፃናት መረጃዎችን ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች እና የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በተሟላ መልኩ መያዛቸውን ክትትል ያላደረገና የመረጃ አያያዝ የአቅም ግንባታ ስልጠና ያልሰጠ መሆኑ፣

134. ህፃናት ለውጭ ጉዲፈቻ ብቁ ናቸው ተብለው ማረጋገጫ የሚሰጣቸው በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ ተሞክሮ ሲሆን፤ በሀገር ውስጥ በሚገኙ ሌሎች አጎራባች ክልሎች በጋዜጣም ሆነ በአማራጭ መገናኛ ዘዴዎች በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ እድሉ ሳይፈለግላቸው መሆኑን፣

## ክፍል አራት

### የማሻሻያ ሀሳቦች

135. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የህፃናት መብትና ደህንነት የሚያስጠብቅ ብሔራዊ ረቂቅ የህፃናት ፓሊሲን በአስቸኳይ ፀድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡
136. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያወጣቸው መመሪያዎች በሁሉም ህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በተሟላ ሁኔታ ተሰራጭተው ሊተገበሩ ይገባል፡፡
137. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት እና ከጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ለሚቀርብለት ሪፖርት እና ባዘጋጃቸው የህፃናት ማሳደጊያ እና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች መገምገሚያ ቼክሊስቶች መሰረት ግምገማ ለተደረገላቸው ተቋማት ግብረ-መልስ ሊሰጥ እና በተዋረድ ያሉትም አካላት ግብረ-መልስ የመስጠት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡
138. የህፃናት ማሳደጊያና የጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች ስለሚኖራቸው ግንኙነትና እና ትስስር ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መዘጋጀት አለበት፡፡
139. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዲፈቻ ህፃናት መብትና ደህንነትን በተመለከተ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ሲሰራ ግንዛቤ ያገኘውን ህዝብ ብዛትና በግንዛቤው የመጡትን ውጤቶች መለካት በሚያስችል መልኩ በእያንዳንዱ ዓ.ም ቅደም ተከተል መሰረት በእስታትስቲካዊ አቀራረብ ሴ/ወ እና ድምር በሚል ዳታዎችን ከየክልሉ በማሰባሰብ ማስቀመጥ አለበት፡፡
140. በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ህፃናት ደህንነታቸው መጠበቁን እና የጉዲፈቻ ተጠቃሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ወደ ውጭ የሚሄዱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ህፃናቱ ባሉበት አገራት በአካል በመገኘት ስላደረጉት ጉብኝት ዝርዝር ሪፖርት ሊያቀርቡና ግብረ-መልስ ሊሰጡ ይገባል፣
141. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የጉዲፈቻ ህፃናትን በሚመለከት የሚሰሩ የተለያዩ ድርጅቶች የትብብርና ቅንጅት ሰነዶች ተዘጋጅቶላቸው የሥራ ድርሻቸው ታውቆ ሊሰሩ ይገባል፣
142. የጉዲፈቻ ህፃናትን የሚመለከቱ መረጃዎች መረጃ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት በማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተም /Management Information System/ የተደገፈ መሆን አለበት፣
143. በጉዲፈቻ አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲ አማካኝነት ወደ ውጭ ሀገር ለሄዱ ህፃናት የላከው ድርጅት/ጉዲፈቻ አስፈፃሚው/ በወር፣ በስድስት ወር፣ በዓመትና ህፃኑ 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ በተከታታይ ዓመታት በየዓመቱ ሪፖርቱን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ መላክ አለበት፤እንዲሁም ጉዲፈቻ ስለተደረጉ ህፃናት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርበው ቅጿ ህፃኑ

በጉዲፈቻ እንዲሄድ ለተደረገበት ክልል፣ የህፃናት ጉዳይ ለሚመለከታቸው መ/ቤት እና ህፃኑን ለሰጠው ማሳደጊያ ድርጅቶች እንዲደርሳቸው መደረግ አለበት፡፡

144. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በውጭ ሀገር የሚገኙ የኢትዮጵያ ኢምባሲዎችና ቆንስላ ጽ/ቤቶች በጉዲፈቻ ወደ ውጭ የሄዱ ህፃናትን ሁኔታ የክትትልና የግምገማ ሥራ ስለመሥራታቸው ከሚመለከተው የመንግስት አካል ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲደርሰው ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

145. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ሴክተር መ/ቤቶች የህፃናትን ጉዳይ በእቅድና ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ አካተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለመደገፍና ለመከታተል የሚረዳ ቼክሊስት አዘጋጅቶ የመ/ቤቶቹን የሥራ እንቅስቃሴ ሊከታተል ይገባል፡፡

146. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሮች መካከል የሚደረግ የጉዲፈቻ ህፃናት መረጃዎችን ጉዲፈቻ አስፈፃሚ ኤጀንሲዎች እና የህፃናት ማሳደጊያ ተቋማት በተሟላ መልኩ መያዛቸውን ክትትል ሊያደርግና የመረጃ አያያዝ የአቅም ግንባታ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

147. ህፃናት ለውጭ ጉዲፈቻ ብቁ ናቸው ተብለው ማረጋገጫ የሚሰጣቸው በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ ተሞክሮ ሳይሆን፤ በሀገር ውስጥ በሚገኙ ሌሎች አጎራባች ክልሎች በጋዜጣም ሆነ በአማራጭ መገናኛ ዘዴዎች በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ እድሉ እንዲፈለግላቸው መደረግ አለበት፡፡